# በማዕከላዊ ኢትዮጲያ ክልል መንግስት የሴቶችና ሕፃናት ጉዳይ ቢሮ

# ክልላዊ የተሻሻለ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የስራ አስፈፃሚ መመሪያ

ጥቅምት/2016 ዓ.ም

ወራቤ

# ክፍል አንድ፡
# አጠቃላይ ሁኔታ

## 1.1. መግቢያ

የማዕከላዊ ኢትዮጲያ ክልል የፌደራል መንግስትን ከመሰረቱ 12 ክልሎች መካከል አንዱ ሲሆን በዋናነት በኢትዮጲያ ማዕከላዊ አቅጣጫ የአገሪቱ ክፍል ይገኛል፡፡ ክልሉ በሰሜን፣ በምዕራብ እና በምስራቅ አቅጣጫ ከኦሮሚያ ክልል፣ በደቡብ በኩል የደቡብ ኢትዮጲያ ክልል፣ በደቡብ ምዕራብ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጲያ ህዝቦች ክልል ይዋስናል፡፡ መዋቅርን በተመለከተ በሰባት ዞኖች፣ በሶስት ልዩ ወረዳዎች፣ በ50 ወረዳዎችና በ29 ከተማ አስተዳደሮች የተዋቀረ ነው፡፡ የማዕከላዊ ኢትዮጲያ ክልል 1,515,600 ሄክታር ስፋት ያለው ሲሆን ከአጠቃላይ የኢትዮጲያ ቆዳ ስፋት 1.38% የሚይዝ ነው፡፡ በ1999ዓ.ም ብሄራዊ የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤት መረጃ ፕሮጀክሽን መሰረት በ2015 ዓ.ም 7,390,772 እንደሆነ ይገመታል፡፡ ይህም ከሀገሪቱ አጠቃላይ ህዝብ 6.47 % የሚሸፍን ነው፡፡

በክልሉ ዉስጥ ከሚሰሩ ዘርፈ ብዙ ሥራዎች ዉስጥ ዋንኛው በሕፃናት መብት ደህንነት ማስጠበቅ ጉዳዮች ልዩ ትኩረት የመስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም ህጻናት የማህበረሰቡን ቀጣይነት የሚያረጋግጡ አካላት መሆናቸውና ከአካልና ከአእምሮ ብስለት ውስንነት በመነጨ የሚደርሱባቸውን ውስብስብ ማህበራዊ፤ኢኮኖሚያዊ፤ስነልቦናዊና አካላዊ ችግሮች ለመታደግ ልዩ የህግ ከለላ ስለሚያስፈልጋቸው ነው፡፡

ለሕጻናት ልዩ እንክብካቤና ጥበቃ ማድረግ የግድ የሚለው ሌላው ምክንያት ሕፃናት ለመብት ጥሰትና ጥቃት በከፍተኛ ደረጃ ተጋላጭ የሆኑ መሆናቸው ነው፡፡ የተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በንጽጽር ከሌሎች በበለጠ መልኩ ለጥቃት ተጋላጭ ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር ሕፃናት በልማድ ዝቅ ተደርገው የሚታዩ፣ ብዙውን ጊዜ በኢኮኖሚ ረገድ በሌሎች ጥገኛ የሆኑ እና የስነ-አካላቸው ሁኔታ ለመብት ጥሰትና ጥቃቶች በከፍተኛ ደረጃ ተጋላጭ ያደርጋቸዋል፡፡በመሆኑም በከፍተኛ ሁኔታ ለጥቃት ተጋላጭ ተብለው ከተለዩ የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል ይመደባሉ፡፡
ሕጻናት የነገ ሀገር ተረካቢዎች ከመሆናቸው አንጻር በቤተሰብ ውስጥ ሆነው ከጥቃት ተጠብቀው በመልካም አስተዳደግ እንዲያድጉ ማድረግ ለሁለንተናዊ ሀገራዊ ዕድገት ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ የጠንካራ ህብረተሰብ መኖር ለህጻናት መብት ጥበቃ ወሳኝ እንደሆነ ሁሉ የህጻናት መብት እና ደህንነት በተግባር መረጋገጥ ደግሞ ለጠንካራ ህብረተሰብ መፈጠር መሰረት ነው፡፡ ስለሆነም ህብረተሰቡ በአጠቃላይ ህጻናትን በተመለከተ በጎ አመለካከትና አሰራር የማራመድ እንዲሁም ከቤተሰብ እና ከመንግስት ጎን በመሆን ለመልካም አስተዳደጋቸው ሁኔታዎችን የማመቻቸት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ ሕጻናትን ከሚደርሱባቸው ዘርፈ ብዙ የመብት ጥሰቶች፤ጥቃቶችና በደሎች ለመታደግና ለመጠበቅ የሚያስችሉ በተለያዩ ጊዜያት የፀደቁ አለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ህጎችና ደንቦች አሉ፡፡ ከነዚህም መካከል እ.ኤ.አ ህዳር 20/1989 ኢትዮጵያም በተወከለችበት በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀው የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን (Convention on the right of the child) አንዱና ዋነኛው ነው፡፡

የኢትዮጵያ መንግስትም ለሕጻናት መብቶች ማክበር ካለው ጽኑ እምነት አንፃር ይህንኑ ኮንቬንሽን በ1984 ዓ/ም በአዋጅ ቁጥር10/84 ተቀብሎ አጽድቋል፡፡በኢፌዲሪ ሕገ-መንግስትም በአንቀጽ 36 ላይ የሕጻናትን መብቶችና ደህንነታቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችሉ ድንጋጌዎች

ተቀምጠዋል፡፡ይህም በመሆኑ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን በአሁኑ ወቅት የአገሪቱ የህግ አካል ሆኖ እየተሰራበት ይገኛል፡፡

በዚሁ ኮንቬንሽን መሠረት ህብረተሰቡ ስለ ሕጻናት መብቶች ኮንቬንሽን ያለዉን ግንዛቤ ከፍ በማድረግ ሕፃናት መብትና ደህንነታቸው ተጠብቆ እንዲያድጉ በመከናወን ላይ ያለውን እንቅስቀሴ የበለጠ ለማጎልበት የተለያዩ የአሰራር ስልቶች ተቀይሰው ተግባራዊ እየተደረጉ ሲሆን ከነዚህም ዉስጥ አንዱና ዋነኛዉ ከፌደራል እስከ ቀበሌ ድረስ ተቋቁሞ እንቅስቃሴ እያደረገ ያለው የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ነው፡፡

ይኼው ኮሚቴ በ1995ዓ/ም ተቋቁሞ መንቀሳቀስ የጀመረና የስራ ማስፈፀሚያ መመሪያ በ1997 ዓ/ም ተዘጋጅቶለት በ2000 ዓ/ም እንደገና የተከለሰ ቢሆንም አሁንም የራሱ ውስንነቶች ያሉበት በመሆኑና በየደረጃው ያለውም ኮሚቴ በሚፈለገው መጠን መንቀሳቀስ ባለመቻሉ በጥናት ላይ የተመሰረተና የክልሉን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ መመሪያ መዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ በክልሉ ያለዉን የኮሚቴዉን እንቅስቃሴ በአማካሪ ድርጅት በማስጠናት በአፈጻጸም ወቅት የተከሰቱ ችግሮችን በመለየትና ከ2002 ዓ/ም ጀምሮ የክልሉ መንግስት ባወጣው የሴክተር መ/ቤቶች ስልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 178/2011 መሰረት ከተደራጀዉ ከሴቶች ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ አደረጃጀት ጋር የተጣጣመ የኮሚቴ አደረጃጀትና አሠራር ማንዋል ቢዘጋጅም የክልሉ አስፈፃሚ አካላት አዋጅ ቁጥር 192/2014 በዝርዝር በተቀመጠው ኃላፊነቶች የአደረጃጀት ለውጥ በመደረጉ ለሴቶች ህፃናት ጉዳይ ቢሮ ስልጣን የተሰጠበ መሆኑ አደረጃጀቱ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ መመሪያ በአዲስ መልክ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህ የተሻሻለ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

## 1.2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ በማዕከላዊ ኢትዮጲያ ክልል መንግሥት በሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ቢሮ አደረጃጀት የተዘጋጀ ክልላዊ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ መመሪያ /Guidline / ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

## 1.3. የቃላት ትርጉም

ከዚህ በታች የተጠቀሱት ቃላቶች በመመሪያው ውስጥ የሚከተሉት ትርጉም አላቸው

1. ክልል ማለት፣ የማዕከላዊ ኢትዮጲያ ክልል ማለት ነዉ ፡፡
2. ሕፃን ማለት፣ በዓለም አቀፉ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ድንጋጌ መሠረት እድሜዉ ከ18 ዓመት በታች የሆነ ማንኛዉም ሰዉ ማለት ነዉ ፡፡
3. የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ማለት፣ በተባበሩትመንግስታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ ጸድቆ በሥራ ላይ የዋለና አገራችንም ተቀብላዉ ተግባራዊ በማድረግ ላይ የሚገኘዉ የሕፃናትን ማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ መብቶችን አንድ ላይ አካቶ የያዘ ሰነድ ነዉ ፡፡
4. የሕፃናት መብቶች ኮንቬሽን ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ማለት፣ የህጻናትን ማህበራዊ፤ኢኮኖሚያዊ፤ፖለቲካዊና ባህላዊ መብቶችን ለማስከበርና ህጻናትን ከጥቃት ለመከላከል በክልሉ ዉስጥ በየደረጃዉ እስከ ቀበሌ ድረስ የተቋቋመ ኮሚቴ ማለት ነዉ ፡፡
5. የፆታ ትንታኔ፡- በዚህመመሪያ ዉስጥ በወንድ ፆታ የተገለጸዉ ለሴትም ያገለግላል፡፡

## 1.4. የሕጻናት መብቶች ኮንቬንሽን የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ራዕይ፤ተልዕኮና ዕሴት

### 1.4.1.ራዕይ

በክልሉ ውስጥ የሕጻናት መብቶች ተከብረዉ፣ ህጻናት ከጥቃት ተጠብቀዉ፣ ተገቢዉ እንክብካቤ ተደርጎላቸዉ ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰባቸዉ ጎልብቶና መልካም ዜጋ ሆነዉ የሚያድጉበት ማህበራዊ አካባቢ ተፈጥሮ ማየት ፡፡

### 1.4.2. ተልዕኮ

የኮሚቴው መሠረታዊ ተልዕኮ የሕጻናትን፣የማህበረሰቡንና የመንግስትን ፍላጎት ባማከለ መልኩ የሕጻናት መብቶች ኮንቬንሽን በላቀ ደረጃ እንዲተገበር ማድረግና አፈጻጸሙንም መከታተል፡፡

### 1.4.3. ዕሴት

የኮሚቴው አብይ እሴቶች ህብረተሰቡን በማሳተፍና ቅንጅታዊ አሰራርን በመዘርጋት ጥራት ያለዉ አሳታፊና ሁሉን አቀፍ ተደራሽ የሆነ አገልግሎት መስጠት ነዉ፡፡

## 1.5. ዓላማ

የሕፃናት መብቶች /convention / ላይ የተደነገጉት የህጻናት መብቶች በሁሉም ደረጃ ተግባራዊ ሆነዉ ሕጻናት የመብቶቻቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፤

**ዝርዝር ዓላማዎች**

1. የኮንቬንሽኑ መሰረታዊ ዓላማዎች በሕብረተሰቡ ዘንድ በስፋት እንዲታወቁና እንዲተገበሩ ማድረግ
2. ኮንቬንሽኑን ተግባራዊ ለማድረግ ቁልፍ ሚና የሚጫወቱ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን በመለየት ማስተባበር
3. ከሕጻናት መብትና ደህንነት ጋር የተያያዙ ስራዎችን የሚያከናውኑ መንግስታዊ፣መንግስታዊ ያልሆኑና ማህበረሰብ አቀፍ ድርጅቶች በተቀናጀ መልኩ ሥራቸዉን እንዲያካሂዱ ማገዝ፤ማስተባበርና መደገፍ፣ተግባራዊነቱን መከታተል
4. የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽንን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ስልቶችን በመቀየስ ተግባራዊ እንዲያደረጉ ማድረግና አፈፃፀማቸውን እና የመጣውን ለውጥ መከታተል
5. ለሕፃናት መብት መከበር ምቹ ማህበራዊ አካባቢ እንዲፈጠርና የነቃ ተሳትፎ የሚያደርግ ማህበረሰብ እንዲኖር ጥረት ማድረግ
6. የሕፃናትን የተሻለ እድገት ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረት ውስጥ በንቃት በመሳተፍ ምቹ ማህበራዊ አካባቢ መፍጠር
7. ችግር ፈቺ ጥናቶች፤አውደ ጥናቶችና ሴሚናሮች እንዲካሄዱ ለሚመለከተው አካል ግብዓት መስጠትና ግፊት ማድረግ
8. ከአባል መ/ቤቶችና ከሌሎችም የሚመለከታቸው አካላት የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽንን አስመልክቶ ወቅታዊ የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ማሰባሰብ፤መተንተንና ለበላይ የተጠሪ አካል ማቅረብ ወዘተ ናቸዉ፡፡

## 1.6. የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ምንነት ዝርዝር ትንታኔና ማብራሪያ

በተለያዩ ጊዜያት ሕጻናት የሚገኙበትን አስከፊ ሁኔታ በመገንዘብ መንግስታት በአህጉርና በዓለም አቀፍ ደረጃ የህጻናትን ጉዳይ በማንሳት ሲመክሩና የተለያዩ ብዙ ውሳኔዎችንም ሲያስተላልፍ ቆይተዋል፡፡ በዚህም መሰረት የተባበሩትመንግስታትድርጅትእ.ኤ.አበ1948 ባወጣውአለም አቀፍ የሰብአዊመብቶችድንጋጌ (Universal Declaration on Human Rights) ላይየሕፃናትመብቶችንየሚያስከብሩናከተለያዩጥቃቶችምየሚከላከሉድንጋጌዎችበጉልህእንዲሰፍሩአድ ርጓል፡፡ ይሁን እንጂ በሕጻናት ላይ የሚደርሱ ተፈጥሮአዊ፣ ሰው ሰራሽ ችግሮችንና በደሎች እየሰፉ መምጣታቸውን የተገነዘቡ አገሮች በየአገራቸው የህጻናት መብትና ደህንነትን በተመለከተ ግብረ-ሰናይ ድርጅቶች እንዲቋቋሙ ከማመቻቸት አልፎ ህጻናትን በተመለከተ ዓለም አቀፍ ሕጎች እንዲወጡ ግፊት ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡

እ.ኤ.አ በ1959 ተሻሽሎ የወጣው የጀኔቫ ድንጋጌ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ ባለአስር ነጥብ የሕፃናት መብቶች ድንጋጌ ሆኖ ጸደቀ፡፡ ይህ ድንጋጌ የህጻናት መብቶችን በማስጠበቅ ረገድ ዓለም አቀፍ መመሪያ ሆኖ ለረዥም ጊዜ ሲያገለግል ቢቆይም ከዕለት ወደ ዕለት የህጻናት ችግሮች እየሰፉና እየከፉ በመምጣታቸው የመንግስታትን ትኩረት በመሳባቸው እ.ኤ.አበ1979 ዓለም አቀፍ የሕፃናት በዓል በተከበረበት ወቅት የሕፃናት ጉዳይ እንደገና ተጠንቶ የሕፃናት መብቶች ጉዳይ በኮንቬንሽን መልክ እንዲዘጋጅ በቀረበው ሀሳብ መሰረት ለ10 ዓመታት ጥናት ተደርጎ ረቂቅ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን እ.ኤ.አህዳር 20 /1989 ፀደቀ፡፡ ይህ የጸደቀዉዓለምአቀፍየሕፃናት(54) አንቀጾች ያሉትና በሶስት ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን ክፍል አንድ ከአንቀጽ 1-41 የያዘና አራቱን መሰረታዊ መርሆዎች (አንቀጽ2፣3፣6፣እና 12) አካትቷል ክፍል ሁለት ከአንቀጽ 42-45 የያዘና በድንጋጌው የሰፈሩትን መብቶች አተገባበር የያዘ ሲሆን አገሮች የአፈጻጸም ሪፖርት ማድረግ እንዳለባቸው ያትታል ምሳሌ አንቀጽ 44(1)፡፡ ክፍል ሶስት ከአንቀጽ 46-54 የያዘና አባል ሀገራት ድንጋጌውን የማጽደቅ፤የማሻሻል፤በስራ ላይ ማዋል የመሳሰሉትን ይዟል፡፡

## 1.7. የሕጻናት መብቶች ኮንቬንሽን የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አስፈላጊነት

በሕፃናት ላይ በርካታ የመብት ጥሰቶች የሚፈጸሙ ሲሆን እነዚህ የመብት ጥሰቶች በአብዛኛው ማህበረሰቡ እያየና እየሰማ የሚፈጸሙ ናቸው፡፡ ጥሰቶች በአመዛኙ በሕፃናቱ የቅርብ ዘመዶች፤ ወላጆች፤ ሕጻናቱን እንዲጠብቁና እንዲያስተምሩ ኃላፊነት በተሰጣቸው ግለሰቦችና አካላት ጭምር የሚፈጸም በመሆኑ እነዚህ በአካባቢያችን፤ በቤታችን፤ በጎረቤቶቻችን ወዘተ የሚፈጸሙ የመብት ጥሰቶች ሕጻናት በህይወት ኖረዉ ነገ በአእምሮና በአካል የዳበሩ ዜጎች ሆነዉ አድገው ለራሳቸው፤ ለማህበረሰባቸውና ለሀገር የበኩላቸዉን አስተዋጽኦ እንዳያበረክቱ አሉታዊ ተጽእኖ መፍጠራቸው ለማንም ስውር አይሆንም፡፡

በሕጻናት ላይየሚፈፀሙ ጥቃቶችንና በደሎችን በመከላከልመብታቸዉተጠብቆ ከጥቃትና ከተጽእኖ ነጻ ሆነው አካላዊ፣ ስሜታዊና አእምሮአዊ ፍላጎታቸው ተጠብቆ እንዲያድጉማድረግየእያንዳንዱቤተሰብ ፣ ግለሰብና ማህበረሰብግዴታነዉ፡፡

የሕጻናት መብቶች ኮንቬንሽን የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴን በየደረጃው ማቋቋምና ማጠናከር ያስፈለገበት መሠረታዊ ምክነያት የህጻናትን መብት ተግባራዊ ማድረግና ደህንነታቸውን ማረጋገጥ በአንድ ሴክተር ላይ ብቻ የተጣለ ኃላፊነት ባለመሆኑና የችግሩም አሳሳቢነት ሰፊና

ውስብስብ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ መቀናጀት፣ መተባበርና በጋራ መስራት የግድ የሚል በመሆኑ ነው፡፡

የህጻናት መብቶች አጠቃላይ መርሆዎችን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ቤተሰብ/ወላጆች፣ ማህበረሰብ፣ ማህበራዊ ተቋማት፣ መንግስት....ወዘተየህጻናትን ድጋፍና ክብካቤ ጉዳዮች፣ መሰረታዊ ጤናና ደህንነት፣ ትምህርት፣ ጨዋታ/ተሳትፎ፣ እረፍት፣ ባህላዊ ክዋኔዎች እንደዚሁም የልዩ ጥበቃ ሁኔታዎችን ወዘተ አስመልክቶ በጋራ በመስራት በተሻለና በተቀናጀ ሁኔታ ህጻናትን ለማገልገል የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው መኖር የላቀ አስተዋጽኦ ስለሚኖረው ነው፡፡

በአጠቃላይ ከህጻናት መብቶችና ደህንነቶች ጋር የተያያዙ ተግባራትን በማከናወን ሕፃናትን የመብቶቻቸው ተጠቃሚ ለማድረግ የሚመለከታቸው አካላት በኮሚቴ በመደራጀት መንቀሳቀስ ወሳኝ ስለሆነና በመንግስትም የታመነበት በመሆኑ የህጻናት መብቶች ኮንቬንሽን ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ መኖር ወሳኝ ሆኗል፡፡

## 1.8. የሕጻናት መብቶች ኮንቬንሽን የስራአስፈፃሚኮሚቴውመርሆዎች

በየደረጃው የሚኖሩ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎች የሕፃናት መብቶች አፈፃፀምን አስመልክቶ የራሳቸዉን አስተዋጽኦ ለማበርከት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ዙሪያ የአለም አቀፉን የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽንም ሆነ የአፍሪካ የሕፃናት መብትና ደህንነት ቻርተር አራቱን አብይ መርሆዎች መሰረት ማድረግ የግድ ይላል፡፡ እነዚህ መርሆዎች የሕፃናቱን መብት ለመረዳት፤ለመፈጸምም ሆነ ለመከታተል እንደ ገዥ ህግ የሚወሰዱ ናቸው፡፡ እነዚህም መርሆዎች፣

### 1. አድልዎ ያለማድረግ /የእኩልነት መርሆ/

ኮሚቴዉ በተቋቋመበት አካባቢ ያሉ ሕፃናት በወላጆቻቸዉ ወይም በአሳዳጊዎቻቸው በዘር፤በቀለም፤በጾታ፤በቋንቋ፤በሐይማኖት፤በፖለቲካ፤አመለካከት፤በማህበራዊአመጣጥ፤በሀብት፤ በአካል ጉዳት፤ በትውልድ...ወዘተ ላይ የተመሰረተ ምንም አይነት መድልዎ እንዳይደረግባቸዉ አስፈላጊዉን ሁሉ ያደርጋል፡፡ /የሕፃናት መብቶች ስምምነት አንቀጽ 2 እና የአፍሪካ የህፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር አንቀጽ 3 ያረጋግጣል

### 2. የሕፃናትን ጥቅም ማስቀደም

በአፍሪካ የህጻናት ደኅንነት ቻርተርና የዓለም አቀፍ የህፃናት ኮንቬንሽኑ በሚደነግገዉ መሠረት የህፃናቱን ጥቅም በማስቀደሙ በኩል የድርሻቸዉንይወጣሉ፡፡/ የሕጻናት መብቶች ስምምነት አንቀጽ 3 እና የአፍሪካ የህፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር አንቀጽ 4/ ያረጋግጣል

### 3. በሕይወት የመኖርና የማደግ መብት

የህፃናት በህይወት የመኖርና የማደግ መብት እንዲረጋገጥ ማኅበረሰብ አሳታፊ ሥርዓት በመዘርጋት የሰላ እንቅስቃሴ ያደርጋሉ፡፡ /የሕፃናት መብቶች ስምምነት አንቀጽ 6 እና የአፍሪካ የህፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር አንቀጽ 5/ ያረጋግጣል

### 4. የህጻናት የተሳትፎና ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት

ሕጻናቱ በህፃናት ፓርላማዎች ተሳታፊ እንዲሆኑና ኃሳባቸዉን በነፃነት መግለጽ እንዲችሉ የማበረታታትና ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰባቸዉ እንዲጎለብት ከማድረግ አንጻር ኮሚቴዉ ጉልህ ሚና ይጫወታል፡፡ /የሕፃናት መብቶች ስምምነት አንቀጽ 12(1) እና የአፍሪካ የህጻናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር አንቀጽ 7/ያረጋግጣል

## 1.9. የስራአስፈፃሚኮሚቴውየትግበራስልቶች (Strategies)

ከክልል እስከ ቀበሌ ድረስ የተቋቋመው የህጻናት መብቶች ኮንቬንሽን ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተልዕኮውን እውን ለማድረግ እንዲረዳው የሚከተሉትን ስልቶች ይጠቀማል፡፡

1. የህዝብ ንቅናቄ በመፍጠር ህብረተሰቡ በህጻናት መብቶችና ደህንነት ዙሪያ ያለዉን ግንዛቤ ማሳደግ
2. ቀጣይነት ያለዉ ስልጠናና ትምህርት መስጠት
   - በህጻናት መብትና ደህንነት ዙሪያ የዳሰሳ ጥናት በማድረግ ችግሮችን ለይቶ ማዉጣት
   - ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሠራርን ማጠናከር
   - ጠንካራ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ስርአት መዘርጋት
   - ጠንካራ የክትትልና ግምገማ ስርዐት በመዘርጋት ተገቢዉን ድጋፍ ማድረግ
   - ኃብት ማሰባሰብ /ፕሮጀክት መቅረጽ / ወዘተ

# ክፍል ሁለት

## የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ተጠሪነት፤ውሳኔ አሰጣጥና አደረጃጀት

### 2.1. የህጻናት መብቶች ኮንቬንሽን ኮሚቴዉ ተጠሪነት

1. በክልል፣በዞን፣በልዩወረዳ፣በወረዳ፣በከተማ አስተዳደሮች እና በቀበሌ ደረጃ የሚቋቋሙ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች ተጠሪነታቸዉ በተቋቋሙበት አካባቢ ላለዉ ሴቶችና ህጻናት ጉዳይቢሮ /መምሪያ/ ጽ/ቤትይሆናል፡፡
2. የከተማም ሆነ የገጠር ቀበሌያት የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች ተጠሪነታቸዉ በልዩ ወረዳ፤ በወረዳና በከተማ የሕፃናትን ጉዳይ ለሚከታተለው (የሴቶችና ህጻናት ጽ/ቤት) አካልይሆናል፡፡
3. የወረዳና የከተማ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች ቀጥተኛ ተጠሪነታቸዉ ለወረዳ/ ለከተማ ሴቶችና ህጻናት ጽ/ቤት ሆኖ በተዋረድ ከዞን የህጻናት መብቶች ኮንቬንሽን ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች ጋር ግንኙነት የሚያደርጉ ይሆናል፡፡
4. ከላይ የተዘረዘሩት ተጠሪነቶች እንደ ተጠበቁ ሆነዉ ከክልል እስከ ወረዳ/ከተማ ድረስ ያሉ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች በየደረጃው ካሉ የሕፃናት ጉዳይ ከሚመለከታቸው ቢሮ፤ መምሪያ ወይም ጽ/ቤት ጋር ግንኙነት ማድረግና ተገቢዉን እገዛ ማግኘት የሚኖርባቸዉ ሲሆን የሴቶችና ህጻናት ቢሮ፤ መምሪያ፤ ጽ/ቤት ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

### 2.2. የስብሰባ ሥነ-ሥርዓትና ዉሳኔ አሰጣጥ

የክልል፣ የዞን፣ የልዩ ወረዳ፣ የወረዳ፣ የከተማ አስተዳደርና የቀበሌ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የስብሰባ ስርአት እንደሚከተለዉ ይሆናል፣

1. የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች አስቸኳይ ስብሰባዎችን ሳያካትት በሦስት ወር ይሰበሰባሉ፣ይወያያሉ፡፡
2. አስቸይ ስብሰባ በሚያስፈልግበት ጊዜና በኮሚቴዉ ከግማሽ በላይ( 50+1) አባላት ከታመነበትና ጉዳዩ አንገብጋቢ መሆኑ በኮሚቴዉ ሰብሳቢ ከታመነበት አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡
3. ከሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ውስጥ ከግማሽ በላይ (50+1) አባላት ከተገኙ ምልአተ ጉባኤው እንደተሟ ላይቆጠራል፡፡ ምልዓተ ጉባኤ ካልተሟላ በድጋሚ የስብሰባ ጥሪይ ደረጋል፡፡ በድጋሚ በተደረገው ጥሪ ምልዓተ ጉባኤው ካልተሟላ በተገኙ አባላት ስብሰባው ሊካሄድና ዉሳኔዉ ሊተላለፍ የሚችል ሲሆን በዚህ ስብሰባ የሚተላለፉ ዉኔዎች እንደሌሎቹ የስብሰባ ዉሳኔዎች ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡
4. ለኮሚቴዉ የቀረቡት አጀንዳዎች ለዉሳኔ ቀርበዉ ድምጽ ሲሰጥ አብላጫ ድምጽ ያገኘዉ ሃሳብ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡ ሆኖም የተሰጠዉ ድምጽ እኩል ከሆነ ሰብሳቢዉ ድምጽ የሚሰጠዉ ሃሳብ ተቀባይነት ያገኛል፡፡

5. ለኮሚቴው መደበኛ ስብሰባ ከሶስት የሥራ ቀናት በፊት፣ ለአስቸኳይ ስብሰባ ደግሞ ከአንድ ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አባላት የስብሰባውን አጀንዳ፣ ቦታውን፣ ቀኑንና ሰዓቱን እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡
6. በኮሚቴው መደበኛ ስብሰባ ላይ የተለያዩ ጉዳዮች እንደ ሁኔታው በአጀንዳነት ተይዘው ለውይይት ይቀርባሉ፡፡ በስብሰባው አጀንዳ እንዲያዝለት የሚፈልግ የኮሚቴ አባል ካለ ስብሰባዉ ከመካሄዱ ከአንድ ቀን በፊት ለኮሚቴው ፀኃፊ ወይም ለሰብሳቢው በጽሁፍ ማስታወቅ ይኖርበታል፡፡
7. እያንዳንዱ የኮሚቴው አባል የኮሚቴውን የስብሰባ ጊዜ ያከብራል፣ ያለሰብሳቢው እውቅናም ከስብሰባ አይቀርም፡፡
8. ዝርዝር የስብሰባ ስርአትና መተዳደሪያ ዉስጠ ደንብ ኮሚቴዉ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 2.3. የኮሚቴው አደረጃጀት

### 2.3.1. የክልሉ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ሥራ አስፈጻሚ አብይ ኮሚቴ አደረጃጀት

የክልሉ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ሥራ አስፈጻሚ አብይ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለክልሉ ሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ቢሮ ሆኖ የሚከተሉት ኮሚቴዎች ይኖሩታል

1. የሴቶችና ህጻናት ቢሮ ኃላፊ -----------------------------------------------------------ሰብሣቢ
2. የጤና ቢሮ ኃላፊ -------------------------------------------------------------------ም/ሰብሳቢ
3. ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር --------------------------------------------------------------ፀሀፊ
4. ፍትህ ቢሮ ኃላፊ ------------------------------------------------------------------------አባል
5. ሰላምና ፀጥታ ቢሮ ኃላፊ ---------------------------------------------------------------አባል
6. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ -----------------------------------------------አባል
7. የባህል፣ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ --------------------------------------------------------------አባል
8. የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ----------------------------------------------------------------------አባል
9. ወሳኝ ኩነት መዝገባ ኤጀንሲ ኃላፊ --------------------------------------------------------አባል
10. የመንግስት ኮሚኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ -------------------------------------------------------አባል
11. የትምህርት ቢሮ ኃላፊ ----------------------------------------------------------------------አባል
12. የህጻናት ፓርላማ አፈ-ጉባኤ ---------------------------------------------------------------አባል
13. ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ---------------------------------------------------------አባል
14. ክልል ምክር ቤት ጽ/ቤት ኃላፊ ---------------------------------------------------------አባል
15. ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ኮሚሽነር ------------------------------------------------------አባል
16. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ ኃላፊ ------------------------------------------አባል
17. የውሃ፣ማዕድንና ኢነርጂ ልማት ቢሮ ኃላፊ---------------------------------------------አባል
18. የግብርና ቢሮ ኃላፊ ------------------------------------------------------------------------አባል
19. ርዕሰ መስተዳደር ጽ/ቤት ኃላፊ-------------------------------------------------------------አባል
20. የሥራ እድል ፈጠራና ኢንትርፕራይዝ ልማት ቢሮ ኃላፊ--------------------------------------አባል
21. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ቢሮ ኃላፊ ----------------------------------------አባል
22. የወጣቶች ማህበር ሰብሳቢ --------------------------------------------------------------------አባል
23. የሴቶች ማህበር ሰብሳቢ ---------------------------------------------------------------------አባል

ለስራዉ መቃናት የሚያግዙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን፣ማህበረሰብ አቀፍ ድርጅቶችንና (CBOs) ሌሎች መ/ቤቶችንና ታዋቂ ግለሰቦችን በአባልነት ማቀፍ ይቻላል።

## 2.3.1.1. የክልል የክልሉ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ሥራ አስፈጻሚ አብይ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

የክልሉ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ሥራ አስፈጻሚ አብይ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለክልሉ ሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ቢሮ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል

- በኮንቬንሽኑ መሰረታዊ መርሆችን አቅጣጫ መሰረት በማድረግ በክልል ቴክኒካል ኮሚቴ የተዘጋጀውን ዕቅድ በመገምገም ያፀድቃል፤
- የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስራዎች የማቀናጀትና በተለያዩ ሴክተሮች የልማት ፕሮግራሞችና ዕቅዶች ዉስጥ የማካተት፣ የህፃናት መብቶችን ተግባራትን አጠቃላይ የልማት እቅዶችና መርሀ-ግብሮች አካል አድርጐ በመውሰድ ይመራል፣ ያስተባብራል፤ ይገመግማል፣
- የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን አቅም ለመገንባት የሚረዳ የሀብት ማሰባሰብ እንቅስቃሴን ያስተባብራል፤
- የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የድርጊት መርሀ-ግብርን ለማስፋፋት በጀት ይመድባል፤
- የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ድንጋጌዎች ክልሉ በሚያካሂዳቸው ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ባህላዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዲካተቱ እንዲሁም በሚወጡ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ህፃናት ተጠቃሚና ተሳታፊ መሆናቸውን በመገምገም አቅጣጫ ያስቀምጣል፤
- በክልሉ ውስጥ ከህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ጋር የሚዛመዱ ሥራዎችን የሚያከናውኑ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችንና ተቋማትን ያበረታታል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል።
- ህፃናትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ሁሉ መንግስታዊ ወይም የማህበራዊ ደህንነት ተቋማት፣ፍርድ ቤቶች፣የአስተዳደር ባለስልጣናት፣የህግ አውጪ አካላት እርምጃዎች ሲወስዱ/ዉሳኔ ሲሰጡ /የህግ አግባቡን ተከትለዉ የህፃናት ጥቅምና ደህንነቶች ከማንኛውም ጉዳይ ቅድሚያ እንዲሰጣቸው ያደርጋል።
- የህፃናት የትምህርት ፣የጤና፣ የማህበራዊ ደህንንነትና ሌሎች በኮንቬንሽኑ ውስጥ የተጠቀሱት መብቶች ከማንኛውም በክልሉ ውስጥ ከሚደረጉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ጋር እንዲቀናጁና ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል።
- ሕፃናትን የሀገር ውስጥ ጉዲፈቻና የሕፃናት ማሳደጊያዎች/ማቆያዎች የሚሰጡትን አገልግሎት በሚመለከት የመንግሥትን ደንብና መመሪያ የተከተለ መሆኑን ጉዳዩ ከሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበት በመቀናጀት ይከታተላል፣ይቆጣጠራል፣በአጥፊዎች ላይ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድም ድጋፍ ያደርጋል።
- ከአባል መ/ቤቶች ጋር ግንኙነት ያላቸውን ከህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ጋር የተያያዙ ሥራዎችን የሚያከናውኑ ድርጅቶችንና ተቋማትን እንቅስቃሴ ያግዛል።

- የዞንና፣ የልዩ ወረዳ የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የሥራ አስፈፃሚ አብይ ኮሚቴ የአፈፃፀም ልምድ ልውውጥ ግኑኝነት በመፍጠር የኮሚቴው እንቅስቃሴ ትኩረት እንዲያገኝ ያደርጋል፤
- የክልሉ ሕፃናትን ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊ፣ ባህላዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን አስመልክቶ ጥናት እንዲካሄድ ያደርጋል።ዉጤቱንም ተከትሎ እርምጃ ይወስዳል
- በክልሉ በሚገኝ የፖሊስ ኮሌጅ የትምህርት ስርዓት ውስጥ እንደአንድ የትምህርት አይነት (የህፃናት መብት ደህንነት ማስጠበቅ ጉዳዩችን በተመለከተ ) ትምህርት እንዲሰጥ ያደርጋል
- የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሥራዎች ውጤታማ እንዲሆኑ የክትትልና የግምገማ ስርዓት እንዲዘረጋና የመረጃ አሰባሰብ ስርዓት እንዲጠናከር ያደርጋል፤
- በክልሉ የሕፃናት መብቶች የሥራ አፈፃፀምን ኮሚቴ አስመልክቶ በየስድስት ወሩ እና የአመቱን ማጠቃለያ ሪፖርት ለሴቶች ህጻናትና ጉዳይ ቢሮና ለፌዴራል የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ኮሚቴ ሪፖርት ይገመግማል፤ያቀርባል ።

### 2.3.1.2. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

1. የኮሚቴውን ስራ በበላይነት ይመራል፤መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎችን ይጠራል፣ ከፀሀፊው ጋር በመሆን አጀንዳዎችን ያዘጋጃል።
2. የኮሚቴውን ስብሰባ በሊቀ መንበርነት ይመራል።
3. ለኮሚቴው የሚቀርቡ ጉዳዮችን ቅደም ተከተል በማውጣት ለውይይት እንዲቀርቡ ያደርጋል።
4. በማንኛውም አካል ዘንድ ኮሚቴውን ይወክላል፣የኮሚቴውን ጽ/ቤት በበላይነት ይቆጣጠራል። በኮሚቴው ስም የደብዳቤ ልውውጦች ያደርጋል።
5. ኮንቬንሽኑን አስመልክቶ መንግሥት የሚያወጣቸውን መመሪያዎችና ኮሚቴው የሚያፀድቃቸውን ውሣኔዎች ተግባራዊ ያደርጋል። አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል።
6. በየደረጃዉ የሚገኙ የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎች እንዲጠናከሩ እገዛ ያደርጋል።
7. ከክልሉ፣ዞኖች፣ወረዳዎች፣ልዩ ወረዳዎችና ከተሞች የሚቀርቡ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቶችን መርምሮ ከአስተያየት ጋር ለኮሚቴው እንዲቀርቡ ያደርጋል፣ ኮሚቴው ካጸደቃቸው በኂላ ለሚመለከታቸዉ አካላትም እንዲደርሱ ያደርጋል።
8. የኮሚቴው ስራ እንዲቃና አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል።
9. ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ የሚሰጣቸዉን ሌሎች ተግባራት ያከናዉናል።
10. ከክልሉ ሴቶች ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናዉናል።

### 2.3.1.3. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

1. ሰብሳቢው በማይገኝበት ጊዜ ሰብሳቢውን በመወከል ማህበሩን በበላይነት ይመራል፤
2. ሰብሳቢው ከሌለ የኮሚቴውን ስብሰባ በሊቀ መንበርነት ይመራል
3. ለኮሚቴው የሚቀርቡ ጉዳዮችን ከጸሀፊው ጋር በመሆን ቅደም ተከተል በማውጣት ለውይይትእንዲቀርቡ ለሰብሳቢው ያቀርባል
4. ኮንቬንሽኑን አስመልክቶ መንግሥት የሚያወጣቸውን መመሪያዎችና ኮሚቴው የሚያፀድቃቸውን ውሣኔዎች ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል፡፡
5. በየደረጀው የሚገኙ የህጻናት መብቶቸች ኮንቬንሽን የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች እንዲጠናከሩ እገዛ ያደርጋል፡፡
6. የኮሚቴው ስራ እንዲቃና አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል
7. ሰብሳቢው የሚሰጣቸወም ሌሎች ተግባራት ያከናውናል

### 2.3.1.4. የሥራ አስፈፃሚኮሚቴዉ ፀሀፊ ተግባርና ኃላፊነት

1. የኮሚቴውን ጽ/ቤት ያደራጃል፣ደብዳቤዎችን አርቅቆ ለሰብሳቢው ያቀርባል፣ ስርጭታቸዉንም ይከታተላል፡፡
2. ከምክትል ሰብሳቢው ጋር በመሆን የስብሰባ አጀንዳዎችን አዘጋጅቶ ለሰብሳቢው ያቀርባል፣ቃለ-ጉባኤ ይይዛል፡፡
3. የኮንቬንሽኑን አፈፃፀም አስመልክቶ ከክልሉ የህፃናት መብቶች ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል መ/ቤቶችና ከየዞኑ ኮሚቴዎች የሚላኩ ሪፖርቶችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፡፡
4. ኮንቬንሽኑን በሚመለከት የሚወጡ አዋጆችን፣መመሪያዎችን፣ ደንቦችንና ማቴሪያሎችን ያደራጃል፤ ለሚመለከታቸው ያሰራጫል፡፡የኮሚቴው ስራ በሚመለከት ከሰብሳቢው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

### 2.3.2. የክልል ቴከኒክ ኮሚቴ አደረጃጀት

የክልሉ አቢይ ኮሚቴ አባላት ከሚወክሏቸው መ/ቤቶች፣ ኤጀንሲዎችና ተቋማት ጉዳዩ ሚመለከታቸው የሚወክል ዘርፍ ኃላፊና የዳይሬክቶሬቶች ቡድን የክልል ቴክኒካል ኮሚቴ አባላት ይሆናሉ፡፡ ተጠሪነታቸው ለአብይ ኮሚቴ ሆኖ የሚከተሉ አደረጃጀቶች ይኖሩታል፡፡

1. የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ የህፃናት ዘርፍ ኃላፊ -----------------------------------ሰብሳቢ
2. ከጤና ቢሮ ጉዳዩ የሚመለከተው ዘርፍ ኃላፊ ---------------------------------- ም/ሰብሳቢ
3. ከፖሊስ ኮሚሽን ጉዳዩ የሚመለከተው ዘርፍ ኃላፊ---------------------------------------ፀሐፊ
4. የሴቶችና ህፃናት መብትና ደህንነት ማስጠበቅ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር-------------አባል
5. ከጤና ቢሮ ጉዳዩ የሚመለከተው ዘርፍ ዳይሬክተር-------------------------------------አባል
6. ከፖሊስ ኮሚሽን ጉዳዩ የሚመለከተው ዳይሬክተር---------------------------------------አባል
7. ከትምህርት ቢሮ ጉዳዩ የሚመለከተው ዳይሬክተር-------------------------------------- አባል

8. ከፍትህ ቢሮ ጉዳዩ የሚመለከተው ዳይሬክተር------------------------------------------------አባል
9. ከጠቅላይ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩ የሚመለከተው ዳይሬክተር------------------------አባል
10.ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ጉዳዩ የሚመለከተው ዳይሬክተር-------------------አባል
11.ከወሳኝ ኩነት መዝገባ ኤጀንሲ ጉዳዩ የሚመለከተው ዳይሬክተር--------------------- አባል
12.ከሰላምና ፀጥታ ቢሮ ጉዳዩ የሚመለከተው ዳይሬክተር---------------------------------- አባል
13.ከባህል፤ቱሪዝምና ቢሮ ጉዳዩ የሚመለከተው ዳይሬክተር---------------------------------አባል
14.ከክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚመለከተው ዳይሬክተር-------------------------------አባል
15.ከፋይናንስ ቢሮ ጉዳዩ የሚመለከተው ዳይሬክተር-----------------------------------------አባል
16.ከማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ጉዳዩ የሚመለከተው ዳይሬክት------------------------------አባል
17.ከከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ ጉዳዩ የሚመለከተው ዳይሬክተር--------------- አባል
18.ከውሃ፣ማዕድንና ኢነርጂ ልማት ቢሮ ጉዳዩ የሚመለከተው ዳይሬክተር------------- አባል
19.ከግብርና ቢሮ ጉዳዩ የሚመለከተው ዳይሬክተር------------------------------------------አባል
20.ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ቢሮ ጉዳዩ የሚመለከተው ዳይሬክተር--------አባል
21.ከመንግስት ኮሚኒኬሽን  ቢሮ ጉዳዩ የሚመለከተው ዳይሬክተር------------------------አባል
22.ክልል ምክር ቤት ጽ/ቤት ጉዳዩ የሚመለከተው ዳይሬክተር--------------------------- አባል
23.ርዕሰ መስተዳደር ጽ/ቤት ጉዳዩ የሚመለከተው ዳይሬክተር -----------------------------አባል
24.ከኢንተርፐራይዞችና የኢንዳስትሪ ልማት ቢሮ ጉዳዩ የሚመለከተው ዳይሬክተር.....አባል
25.ከወጣቶች ማህበር ጉዳዩ የሚመለከተው ባለሙያ-----------------------------------------አባል
26.ከሴቶች  ማህበር ጉዳዩ የሚመለከተው ባለሙያ--------------------------------------- አባል

2.3.2.1. **የክልል ቴክኒካል ኮሚቴ ተግባርና ሀላፊነት**

- በየደረጃው የተዘጋጁ ዕቅዶችን መሰረት በማድረግ የክልሉን ቴክኒካል ኮሚቴ ዕቅድ አዘጋጅቶ ለአብይ  ኮሚቴ ያቀርባል፤
- በህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትና የህፃናት መብቶች ተጠቃሚነትና ተሳታፊነትን የሚያረጋግጡ አካላት ስለ ኮንቬንሽኑ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፣
- ሕብረተሰቡ ስለህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ተግባራዊነትና አፈፃፀም ግንዛቤ እንዲኖረውና በየአካባቢዉ በህጻናት ላይ የሚደርሱ የተለያዩ ጥቃቶች እንዲቆሙ ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች በየደረጃዉ ይሰራል፡፡
- በየደረጃው የህፃናት ተጋላጭነትን በመከላከልና ተጋላጭ የሆኑ ህፃናት  መብቶች ተፈፃሚነትን በመደገፍና በማቋቋም ረገድ የሚሰሩና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን የማስፈፀም አቅም ማጎልበት፣
- ከህፃናት ኮንቬንሽን ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎች  ሥራ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ምርጥ ተሞክሮዎችን በማሰባሰብና በመቀመር  ለሚመለከታቸው ማድረስና የልምድ ልውውጥ የጉብኝት ኘሮግራሞችን ያመቻቻል፣
- ከሚመለከታቸው የመንግሥት መ/ቤቶች፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ግንኙነት እንዲጠናከር በትብብር ይሰራል፤

- የህፃናት መብቶች ተጠቃሚነታቸውንና ተሳታፊነታቸው እንዲሁም በህፃናት የሚደርሱ ጥቃቶች በህብረተሰቡ ተሳትፎ እንዲፈታ የተለያዩ የህዝብ መገናኛዎችንና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ውጤቶችን የመጠቀም ልምድ በማስፋፋት የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ የሚያስችሉ. ተግባራትን ያከናውናል፣
- በተለያየ ደረጃ ለሚተገበረው መርሀ ግብር አስፈላጊውን የተቀናጀ የቴክኒካል ድጋፍ ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል፣ይከታተላል፣
- በየ3 ወራት የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ክልላዊ ሪፖርት ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ያዘጋጃል፣
- ከአብይ ኮሚቴ ተጨማሪ የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናሉ

### 2.3.3. የዞን/የልዩ ወረዳ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የሥራ አስፈፃሚ አብይ ኮሚቴ አደረጃጀት

የዞኑ/ልዩ ወረዳ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ሥራ አስፈጻሚ አብይ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለዞኑ/ልዩ ወረዳ ሴቶችና ህጻናት ጉዳይ መምሪያ/ጽ/ቤት ሆኖ የሚከተሉት ኮሚቴዎች ይኖሩታል

1. የሴቶችና ህጻናት ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ ------------------------------------------ሰብሣቢ
2. የጤና መምሪያ ኃላፊ ----------------------------------------------------------ም/ሰብሳቢ
3. ፖሊስ መምሪያ ኃላፊ-------------------------------------------------------------ፀሀፊ
4. ፍትህ መምሪያ ኃላፊ-------------------------------------------------------------አባል
5. ሰላምና ፀጥታ መምሪያ ኃላፊ-----------------------------------------------------አባል
6. የሠራተኛና ማህበራዊ መምሪያ ኃላፊ-----------------------------------------------አባል
7. የባህል፣ቱሪዝም መምሪያ ኃላፊ---------------------------------------------------አባል
8. የፋይናንስ መምሪያ ኃላፊ---------------------------------------------------------አባል
9. የትምህርት መምሪያ ኃላፊ--------------------------------------------------------አባል
10. የህጻናት ፓርላማ አፈ-ጉባኤ ----------------------------------------------------አባል
11. ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት -------------------------------------------------አባል
12. የዞኑ አስተዳደር ጽ/ቤት ኃላፊ--------------------------------------------------አባል
13. የዞኑ/ልዩ ወረዳ ምክር ቤት ጽ/ቤት ኃላፊ ----------------------------------------አባል
14. ማረሚያ ተቋም ኃላፊ -----------------------------------------------------------አባል
15. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ ኃላፊ-------------------------------------አባል
16. የኢንተርፕራይዞችና የኢንዳስትሪ ልማት መምሪያ ኃላፊ --------------------------አባል
17. የውሃ፣ማዕድንና ኢነርጂ ልማት መምሪያ ኃላፊ-------------------------------------አባል
18. የግብርና መምሪያ ኃላፊ----------------------------------------------------------አባል
19. የቴክኒክና ሙያ ተቋም ኃላፊ ---------------------------------------------------አባል
20. የወጣቶች ማህበር ሰብሳቢ -------------------------------------------------------አባል
21. የሴቶች ማህበር ሰብሳቢ ---------------------------------------------------------አባል

ለስራዉ መቃናት የሚያግዙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን፣ማህበረሰብ አቀፍ ድርጅቶችንና (CBOs) ሌሎች መ/ቤቶችንና ታዋቂ ግለሰቦችን በአባልነት ማቀፍ ይቻላል

### 2.3.3.1. የዞን/ልዩ ወረዳ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ሥራ አስፈጻሚ አብይ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

የዞን/ልዩ ወረዳ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ሥራ አስፈጻሚ አብይ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለዞኑ/ልዩ ወረዳ ሴቶችና ህጻናት ጉዳይ መምሪያ/ጽ/ቤት ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል

- በኮንቬንሽኑ መሰረታዊ መርሆችን አቅጣጫ መሰረት በማድረግ በዞኑ/ልዩ ወረዳ ቴክኒካል ኮሚቴ የተዘጋጀውን ዕቅድ በመገምገም ያፀድቃል፤
- የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስራዎች የማቀናጀትና በተለያዩ ሴክተሮች የልማት ፕሮግራሞችና ዕቅዶች ዉስጥ የማካተት፣ የህፃናት መብቶችን ተግባራትን አጠቃላይ የልማት እቅዶችና መርሀ-ግብሮች አካል አድርጐ በመውሰድ ይመራል፣ ያስተባብራል፤ ይገመግማል፣
- የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን አቅም ለመገንባት የሚረዳ የሀብት ማሰባሰብ እንቅስቃሴን ያስተባብራል፤
- የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የድርጊት መርሀ-ግብርን ለማስፋፋት በጀት ይመድባል፤
- የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ድንጋጌዎች ክልሉ በሚያካሂዳቸው ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ባህላዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዲካተቱ እንዲሁም በሚወጡ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ህፃናት ተጠቃሚና ተሳታፊ መሆናቸውን በመገምገም አቅጣጫ ያስቀምጣል፤
- በዞኑ/ልዩ ወረዳ ውስጥ ከህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ጋር የሚዛመዱ ሥራዎችን የሚያከናውኑ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችንና ተቋማትን ያበረታታል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል።

- ህፃናትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ሁሉ መንግስታዊ ወይም የማህበራዊ ደህንነት ተቋማት፣ፍርድ ቤቶች፣የአስተዳደር ባለስልጣናት፣የህግ አውጪ አካላት እርምጃዎች ሲወስዱ/ዉሳኔ ሲሰጡ / የህግ አግባቡን ተከትለዉ የህፃናት ጥቅምና ደህንነቶች ከማንኛውም ጉዳይ ቅድሚያ እንዲሰጣቸው ያደርጋል።
- የህፃናት የትምህርት ፣የጤና፣ የማህበራዊ ደህንንነትና ሌሎች በኮንቬንሽኑ ውስጥ የተጠቀሱት መብቶች ከማንኛውም በክልሉ ውስጥ ከሚደረጉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ጋር እንዲቀናጁና ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል።
- የሕፃናትን የሀገር ውስጥ ጉዲፈቻና የሕፃናት ማሳደጊያዎች/ማቆያዎች የሚሰጡትን አገልግሎት በሚመለከት የመንግሥትን ደንብና መመሪያ የተከተለ መሆኑን ጉዳዩ ከሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበት በመቀናጀት

ይከታተላል፣ይቆጣጠራል፣በአጥፊዎች ላይ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድም ድጋፍ ያደርጋል።

- ከአባል መ/ቤቶች ጋር ግንኙነት ያላቸውን ከህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ጋር የተያያዙ ሥራዎችን የሚያከናውኑ ድርጅቶችንና ተቋማትን እንቅስቃሴ ያግዛል።
- የወረዳና ቀበሌ የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የሥራ አስፈፃሚ አብይ ኮሚቴ የአፈፃፀም ልምድ ልውውጥ ግኑኝነት በመፍጠር የኮሚቴው እንቅስቃሴ ትኩረት እንዲያገኝ ያደርጋል፤
- የዞኑ/ልዩ ወረዳ ሕፃናትን ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊ፣ ባህላዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን አስመልክቶ ጥናት እንዲካሄድ ያደርጋል። ዉጤቱንም ተከትሎ እርምጃ ይወስዳል
- የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሥራዎች ውጤታማ እንዲሆኑ የክትትልና የግምገማ ስርዓት እንዲዘረጋና የመረጃ አሰባሰብ ስርዓት እንዲጠናከር ያደርጋል፤
- በዞኑና ልዩ ወረዳ የሕፃናት መብቶች የሥራ አፈፃፀምን ኮሚቴ አስመልከቶ በየስድስት ወሩ እና የአመቱን ማጠቃለያ ሪፖርት ለዞኑ/ልዩ ወረዳ ሴቶች ህጻናትና ጉዳይ መምሪያ/ጽ/ቤት እና ለክልሉ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ኮሚቴ ሪፖርት ይገመግማል፤ያቀርባል ።

### 2.3.3.2. የስራ አስፈፃሚ አቢይ ኮሚቴ ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

1. የኮሚቴውን ስብሰባዎች ይጠራል።
2. ከፀሀፊው ጋር በመሆን አጀንዳዎችን ያዘጋጃል።
3. የኮሚቴውን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል።
4. ለኮሚቴው የሚቀርቡ ጉዳዮችን ቅደም ተከተል በማውጣት ለውይይት እንዲቀርቡ ለፀሀፊው በአጀንዳነት ያስይዛል።
5. በማንኛውም አካል ዘንድ ኮሚቴውን ይወክላል፣የኮሚቴውን ጽ/ቤት በበላይነት ይቆጣጠራል፣በኮሚቴው ስም የደብዳቤ ልውውጦች ያደርጋል።
6. ኮንቬንሽኑን አስመልክቶ መንግሥት የሚያወጣቸውን መመሪያዎችና ኮሚቴው የሚያፀድቃቸውን ውሣኔዎች ተግባራዊ ያደርጋል፣አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል።
7. የኮሚቴው ስራ እንዲቃና አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል።
8. የዞን/የልዩ ወረዳ የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎች እንዲጠናከሩ እገዛ ያደርጋል።
9. ከወረዳዎችና ከከተሞች/ቀበሌዎች የሚቀርቡ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቶችን መርምሮ ከአስተያየት ጋር ለኮሚቴው እንዲቀርቡ ያደርጋል። ለሚመለከታቸዉ አካላትም ያሰራጫል።
10. ከክልሉ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰጡትን ተጨማሪ ተግባራት ያከናዉናል።

2.3.3.3. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ ተግባርና ሃላፊነት

1. ሰብሳቢው በማይገኝበት ጊዜ ሰብሳቢውን በመወከል ኮሚቴውን በበላይነት ይመራል፡፡

2. ሰብሳቢው ከሌለ የኮሚቴውን ሰብሰባ በሊቀ መንበርነት ይመራል፡፡

3. ለኮሚቴው የሚቀርቡ ጉዳዮችን ከጸሀፊው ጋር በመሆን ቅደም ተከተል በማውጣት ለውይይት እንዲቀርቡ ለሰብሳቢው ያቀርባል፡፡

4. ኮንቬንሽኑን አስመልክቶ መንግስት የሚያወጣቸውን መመሪያዎችና ኮሚቴው የሚያጸድቃቸውን ውሳኔዎች ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ አፈጻጸማቸውንም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

5. በየደረጀው የሚገኙ የህጻናት መብቶች ኮንቬንሽን የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች እንዲጠናከሩ እገዛ ያደርጋል፡፡

6. የኮሚቴው ስራ እንዲቃና አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል

7. ሰብሳቢው የሚሰጣቸውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል

2.3.3.4. የሥራአስፈፃሚኮሚቴዉፀሀፊተግባርናኃላፊነት

1. የኮሚቴውን ጽ/ቤት ያደራጃል፣ደብዳቤዎችን አርቅቆ ለሰብሳቢው ያቀርባል፣ስርጭታቸዉንም ይከታተላል፡፡
2. ከምክትል ሰብሳቢው ጋር በመሆን የስብሰባ አጀንዳዎችን አዘጋጅቶ ለሰብሳቢው ያቀርባል፣ቃለ-ጉባኤ ይይዛል፡፡
3. የኮንቬንሽኑን አፈፃፀም አስመልክቶ ከክልሉ ከወረዳና ከከተሞች/ቀበሌዎች የህጻናት መብቶች ኮንቬንሽን ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎችና አባል መ/ቤቶች የሚላኩ ሪፖርቶችን ያሰባስባል፣ያጠናቅራል፡፡ ለሚመለከታቸው ያሰራጫል፡፡
4. ኮንቬንሽኑን በሚመለከት የሚወጡ አዋጆችን፣መመሪያዎችን፣ደንቦችንና ማቴሪያሎችን ያደራጃል፤ለሚመለከታቸው ያሰራጫል፡፡የኮሚቴው ስራ በሚመለከት ከሰብሳቢው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

### 2.3.4. የዞን/ልዩ ወረዳ ቴከኒክ ኮሚቴ አደረጃጀት

የዞኑ/ልዩ ወረዳ አቢይ ኮሚቴ አባላት ከሚወክሏቸው መምሪያዎችና ጽ/ቤት ፣ ተቋማት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ዘርፍ ኃላፊና የአስተባባሪ ቡድን የዞኑ/ልዩ ወረዳ ቴክኒካል ኮሚቴ አባላት ይሆናሉ፡፡ ተጠሪነታቸው ለአብይ ኮሚቴ ሆኖ የሚከተሉ አደረጃጀቶች ይኖሩታል፡፡

1. የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ መምሪያ/ጽ/ቤት የህፃናት ዘርፍ ም/ኃላፊና የሴቶችና ህፃናት መብትና ደህንነት ማስጠበቅ ማስተባበሪያ/ ቡድን መሪ ---------------------------ሰብሳቢ
2. ከጤናመምሪያ ጉዳዩ የሚመለከተው ዘርፍ ም/ኃላፊ/ማስተባበሪያ/ ቡድን መሪ …………..... ም/ሰብሳቢ
3. ከፖሊስ መምሪያ ጉዳዩ የሚመለከተው ዘርፍ ም/ኃላፊ/ማስተባበሪያ/ ቡድን መሪ ፀሐፊ
4. ከትምህርት መምሪያ ጉዳዩ የሚመለከተው አስተባባሪ …………………………………. አባል
5. ከፍትህ መምሪያ ጉዳዩ የሚመለከተው ማስተባበሪያ/ ቡድን መሪ ………………… አባል
6. ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩ የሚመለከተው ማስተባበሪያ/ ቡድን መሪ …………….. አባል
7. ከሠ/ማ/ ጉዳይ መምሪያ ጉዳዩ የሚመለከተው ማስተባበሪያ/ ቡ/ መሪ……………. አባል
8. ከወሳኝ ኩነት መዝገባ መምሪያ ጉዳዩ የሚመለከተው ማስተባበሪያ/ ቡ/ መሪ . አባል
9. ከሰላምና ፀጥታ መምሪያ ጉዳዩ የሚመለከተው ማስተባበሪያ/ ቡድን መሪ ………. አባል
10. ከባህል፣ቱሪዝምና መምሪያ ጉዳዩ የሚመለከተው ማስተባበሪያ/ ቡ/ መሪ ………. አባል
11. ከፋይናንስ መምሪያ ጉዳዩ የሚመለከተው ማስተባበሪያ/ ቡድን መሪ ……………. አባል
12. ከማረሚያ ቤቶች ተቋም ጉዳዩ የሚመለከተው ማስተባበሪያ/ ቡድን መሪ …….. አባል
13. ከ/ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ ጉዳዩ የሚመለከተው ማስተባበሪያ/ ቡ/ መሪ. አባል
14. ከውሃ፣ማዕድንና ኢነርጂ ልማት መ/ ጉዳዩ የሚመለከተው ማስተባበሪያ/ ቡ/ መሪ አባል
15. ከግብርና መምሪያ ጉዳዩ የሚመለከተው ማስተባበሪያ/ ቡድን መሪ …………….. አባል
16. ከቴክኒክና ሙያ ተቋም ጉዳዩ የሚመለከተው ማስተባበሪያ/ ቡድን መሪ ………. አባል

#### 2.3.4.1. የዞን/ልዩ ወረዳ ቴክኒካል ኮሚቴ ተግባርና ሀላፊነት

- በየደረጃው የተዘጋጁ ዕቅዶችን መሰረት በማድረግ የዞኑና ልዩ ወረዳ ቴክኒካል ኮሚቴ ዕቅድ አዘጋጅቶ ለአብይ ኮሚቴ ያቀርባል፣
- በህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትና የህፃናት መብቶች ተጠቃሚነትና ተሳታፊነትን የሚያረጋግጡ አካላት ስለ ኮንቬንሽኑ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፣
- ሕብረተሰቡ ስለህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ተግባራዊነትና አፈፃፀም ግንዛቤ እንዲኖረውና በየአካባቢዉ በህጻናት ላይ የሚደርሱ የተለያዩ ጥቃቶች እንዲቆሙ ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች በየደረጃዉ ይሰራል፡፡

- በየደረጃው የህፃናት ተጋላጭነትን በመከላከልና ተጋላጭ የሆኑ ህፃናት መብቶች ተፈፃሚነትን በመደገፍና በማቋቋም ረገድ የሚሰሩና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን የማስፈፀም አቅም ማጎልበት፣
- ከህፃናት ኮንቬንሽን ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎች ሥራ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ምርጥ ተሞክሮዎችን በማሰባሰብና በመቀመር ለሚመለከታቸው ማድረስና የልምድ ልውውጥ የጉብኝት ኘሮግራሞችን ያመቻቻል፣
- ከሚመለከታቸው የመንግሥት መ/ቤቶች፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ግንኙነት እንዲጠናከር በትብብር ይሰራል፤
- የህፃናት መብቶች ተጠቃሚነታቸውንና ተሳታፊነታቸው እንዲሁም በህፃናት የሚደርሱ ጥቃቶች በህብረተሰቡ ተሳትፎ እንዲፈታ የተለያዩ የህዝብ መገናኛዎችንና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ውጤቶችን የመጠቀም ልምድ በማስፋፋት የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ የሚያስችሉ. ተግባራትን ያከናውናል፣
- በተለያየ ደረጃ ለሚተገበረው መርሀ ግብር አስፈላጊውን የተቀናጀ የቴክኒካል ድጋፍ ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል፣ይከታተላል፣
- በየ3 ወራት የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ዞን/ልዩ ወረዳ ሪፖርት ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ያዘጋጃል፣
- ከአብይ ኮሚቴ ተጨማሪ የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናሉ

### 2.3.5. የወረዳ / ከተማ አስተዳደር የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የሥራ አስፈፃሚ አብይ ኮሚቴ አደረጃጀት

የወረዳ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ሥራ አስፈጻሚ አብይ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለወረዳ ሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ጽ/ቤት ሆኖ የሚከተሉት ኮሚቴዎች ይኖሩታል

1. የሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊ ----------------------------------------ሰብሣቢ
2. የጤና ጽ/ቤት ኃላፊ ---------------------------------------------------ም/ሰብሳቢ
3. ፖሊስ ጽ/ቤት ኃላፊ----------------------------------------------------------------ፀሀፊ
4. ፍትህ ጽ/ቤት ኃላፊ---------------------------------------------------------------አባል
5. ሰላምና ፀጥታ ጽ/ቤት ኃላፊ-------------------------------------------------------አባል
6. የሠራተኛና ማህበራዊ ጽ/ቤት ኃላፊ-----------------------------------------------አባል
7. የባህል፤ቱሪዝም ጽ/ቤት ኃላፊ-----------------------------------------------------አባል
8. የፋይናንስ ጽ/ቤት ኃላፊ-----------------------------------------------------------አባል
9. ወሳኝ ኩነት መዝገባ ጽ/ቤት ኃላፊ--------------------------------------------------አባል
10. የትምህርት ጽ/ቤት ኃላፊ---- ------------------------------------------------------አባል
11. የህጻናት ፓርላማ አፈ-ጉባኤ ------------------------------------------------------------አባል
12. የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት --------------------------------------አባል
13. የወረዳ ምክር ቤት ጽ/ቤት ኃላፊ ----------------------------------------------------አባል
14. የወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት ኃላፊ ------------------------------------------------አባል
15. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ጽ/ቤት ኃላፊ--------------------------------------አባል
16. የውሃ፣ማዕድንና ኢነርጂ ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ--------------------------------አባል
17. የግብርና ጽ/ቤት ኃላፊ---------------------------------------------------------------------አባል
18. የወጣቶች ማህበር ሰብሳቢ -------------------------------------------------------------አባል
19. የሴቶች ማህበር ሰብሳቢ ----------------------------------------------------------------አባል

ለስራዉ መቃናት የሚያግዙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን፣ማህበረሰብ አቀፍ ድርጅቶችንና (CBOs) ሌሎች መ/ቤቶችንና ታዋቂ ግለሰቦችን በአባልነት ማቀፍ ይቻላል

#### 2.3.5.1. የወረዳ / ከተማ አስተዳደር የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ሥራ አስፈጻሚ አብይ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

የወረዳ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ሥራ አስፈጻሚ አብይ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለወረዳ/ከተማ አስተዳደር ሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ጽ/ቤት ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል

- በኮንቬንሽኑ መሰረታዊ መርሆችን አቅጣጫ መሰረት በማድረግ በወረዳ ቴክኒካል ኮሚቴ የተዘጋጀውን ዕቅድ በመገምገም ያፀድቃል፤
- የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስራዎች የማቀናጀትና በተለያዩ ሴክተሮች የልማት ፕሮግራሞችና ዕቅዶች ዉስጥ የማካተት፣ የህፃናት መብቶችን ተግባራትን አጠቃላይ የልማት እቅዶችና መርሀ-ግብሮች አካል አድርጐ በመውሰድ ይመራል፣ ያስተባብራል፤ ይገመግማል፣

- የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ  አባላትን አቅም ለመገንባት የሚረዳ የሀብት ማሰባሰብ እንቅስቃሴን ያስተባብራል፤
- የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የድርጊት መርሀ-ግብርን ለማስፋፋት በጀት ይመድባል፤
- የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ድንጋጌዎች ክልሉ በሚያካሂዳቸው ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ባህላዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዲካተቱ እንዲሁም በሚወጡ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች  ህፃናት ተጠቃሚና ተሳታፊ መሆናቸውን  በመገምገም አቅጣጫ ያስቀምጣል፤
- በወረዳ  ውስጥ ከህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ጋር የሚዛመዱ ሥራዎችን የሚያከናውኑ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችንና ተቋማትን ያበረታታል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል።

- ህፃናትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ሁሉ መንግስታዊ ወይም የማህበራዊ ደህንነት ተቋማት፣ፍርድ ቤቶች፣የአስተዳደር ባለስልጣናት፣የህግ አውጪ አካላት እርምጃዎች ሲወስዱ/ዉሳኔ ሲሰጡ / የህግ አግባቡን ተከትለዉ የህፃናት ጥቅምና ደህንነቶች ከማንኛውም ጉዳይ ቅድሚያ እንዲሰጣቸው ያደርጋል።
- የህፃናት የትምህርት ፣የጤና፣ የማህበራዊ ደህንነትና ሌሎች በኮንቬንሽኑ ውስጥ የተጠቀሱት መብቶች ከማንኛውም በክልሉ ውስጥ ከሚደረጉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ጋር እንዲቀናጁና ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል።
- የሕፃናትን የሀገር ውስጥ ጉዲፈቻና የሕፃናት ማሳደጊያዎች/ማቆያዎች የሚሰጡትን አገልግሎት በሚመለከት የመንግሥትን ደንብና መመሪያ የተከተለ መሆኑን ጉዳዩ ከሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበት በመቀናጀት ይከታተላል፣ይቆጣጠራል፣በአጥፊዎች ላይ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድም ድጋፍ ያደርጋል።
- ከአባል መ/ቤቶች ጋር ግንኙነት ያላቸውን ከህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ጋር የተያያዙ ሥራዎችን የሚያከናውኑ ድርጅቶችንና ተቋማትን እንቅስቃሴ ያግዛል።
- የቀበሌ የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የሥራ አስፈፃሚ አብይ ኮሚቴ የአፈፃፀም ልምድ ልውውጥ ግኑኝነት በመፍጠር የኮሚቴው  እንቅስቃሴ ትኩረት እንዲያገኝ ያደርጋል፤
- የወረዳ/ከተማ አስተዳደር ሕፃናትን ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊ፣ ባህላዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን አስመልክቶ  የተደራጁ መረጃዎችን ለሚመለከተው አካል በመቅረብ ውሳኔዎች እንዲያገኙ ያደርጋል።
- የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሥራዎች ውጤታማ እንዲሆኑ የክትትልና የግምገማ ስርዓት እንዲዘረጋና የመረጃ አሰባሰብ ስርዓት እንዲጠናከር ያደርጋል፤
- በወረዳ/ከተማ አስተዳደር  የሕፃናት መብቶች የሥራ አፈፃፀምን ኮሚቴ አስመልክቶ በየስድስት ወሩ እና የአመቱን ማጠቃለያ ሪፖርት ለወረዳ/ከተማ አስተዳደር  ሴቶች ህጻናትና ጉዳይ ጽ/ቤት እና ለዞኑ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል ።

2.3.5.2. የስራአስፈፃሚኮሚቴሰብሳቢተግባርናኃላፊነት

1. የኮሚቴውን ስብሰባዎች ይጠራል፡፡ ከፀሀፊው ጋር በመሆን አጀንዳዎች ያዘጋጃል፡፡
2. የኮሚቴውን ስብሰባ በሊቀ መንበርነት ይመራል፡፡
3. ለኮሚቴው የሚቀርቡ ጉዳዮችን ቅደም ተከተል በማውጣት ለውይይት እንዲቀርቡ ለፀሀፊው በአጀንዳነት ያስይዛል፡፡
4. በማንኛውም አካል ዘንድ ኮሚቴውን ይወክላል፡፡ የኮሚቴውን ጽ/ቤት በበላይነት ይቆጣጠራል፡፡ በኮሚቴው ስም የደብዳቤ ልውውጦች ያደርጋል፡፡
5. ኮንቬንሽኑን አስመልክቶ መንግሥት የሚያወጣቸውን መመሪያዎችና ኮሚቴው የሚያፀድቃቸውን ውሣኔዎች ተግባራዊ ያደርጋል፣ አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል፡፡
6. የኮሚቴው ስራ እንዲቃና አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል፡፡
7. የወረዳው/የከተማው አስተዳደር የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎች እንዲጠናከሩ እገዛ ያደርጋል፡፡
8. ከከተማ/ቀበሌዎች የሚቀርቡ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቶችን መርምሮ ከአስተያየት ጋር ለኮሚቴው እንዲቀርቡ ያደርጋል፡፡
9. እንደ አስፈላጊነቱ ኮሚቴው የሚሰጠውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡
10. ከዞን/ከልዩ ወረዳው የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰጡትን ተጨማሪ ተግባራት ያከናዉናል፡፡

2.3.5.3. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ ተግባርና ሃላፊነት

1. ሰብሳቢው በማይገኝበት ጊዜ ሰብሳቢውን በመወከል ኮሚቴውን በበላይነት ይመራል
2. ሰብሳቢው ከሌለ የኮሚቴውን ሰብሰባ በሊቀ መንበርነት ይመራል
3. ለኮሚቴው የሚቀርቡ ጉዳዮችን ከጸሀፊው ጋር በመሆን ቅደም ተከተል በማውጣት ለውይይት እንዲቀርቡ ለሰብሳቢው ያቀርባል
4. ኮንቬንሽኑን አስመልክቶ መንግስት የሚያወጣቸውን መመሪያዎችና ኮሚቴው የሚያጸድቃቸውን ወሳኔዎች ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ አፈጻጸማቸውንም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
5. በየደረጀው የሚገኙ የህጻናት መብቶች ኮንቬንሽን የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች እንዲጠናከሩ እገዛ ያደርጋል
6. የኮሚቴው ስራ እንዲቃና አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል
7. ሰብሳቢው የሚሰጣቸውንም ሌሎች ተግባራት ያከናወናል

2.3.5.4. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ፀሀፊተግባራት

1. የኮሚቴውን ጽ/ቤት ያደራጃል፣ ደብዳቤዎችን አርቅቆ ለሰብሳቢውና ለምክትል ሰብሳቢው ያቀርባል፣ ስርጭታቸውንም ይከታተላል፡፡

2. ከምክትል ሰብሳቢው ጋር በመሆን የስብሰባ አጀንዳዎችን አዘጋጅቶ ለሰብሰባው ያቀርባል፣ቃለ-ጉባኤ ይይዛል፡፡

3. የኮንቬንሽኑን አፈፃፀም አስመልክቶ ከክልሉ ከወረዳና ከከተሞች/ቀበሌዎች የህጻናት መብቶች ኮንቬንሽን ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎችና አባል መ/ቤቶች የሚላኩ ሪፖርቶችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፡፡ለሚመለከታቸው ያሰራጫል፡፡
4. ኮንቬንሽኑን በሚመለከት የሚወጡ አዋጆችን፣መመሪያዎችን፣ ደንቦችንና ማቴሪያሎችን ያሰራጫል፡፡
5. የኮሚቴውንስራ በሚመለከት ከሰብሳቢው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

### 2.3.5.5. የወረዳ/ከተማ አስተዳደር ቴከኒክ ኮሚቴ አደረጃጀት

የወረዳ/ከተማ አስተዳደር  አቢይ ኮሚቴ አባላት ከሚወክሏቸው ጽ/ቤት ፣ ተቋማት ጉዳዩ የሚመለከታቸው  የቡድን መሪ የወረዳ ቴክኒካል ኮሚቴ አባላት ይሆናሉ፡፡ ተጠሪነታቸው ለአብይ ኮሚቴ ሆኖ የሚከተሉ አደረጃጀቶች ይኖሩታል፡፡

1. የሴ/ ህፃናት ጉዳይ ጽ/ቤት የሴቶችና ህፃናት መብትና ደህንነት ማስጠበቅ ቡ/ መሪ.....ሰብሳቢ
2. ከጤና ጽ/ቤት ጉዳዩ የሚመለከተው ቡድን መሪ ……………………….……...... ም/ሰብሳቢ
3. ከፖሊስ ጽ/ቤት ጉዳዩ የሚመለከተው ቡድን መሪ ……………………………....... ፀሐፊ
4. ከትምህርት ጽ/ቤት ጉዳዩ የሚመለከተው ቡድን መሪ ……………………… …....... አባል
5. ከፍትህ ጽ/ቤት ጉዳዩ የሚመለከተው ቡድን መሪ .............................................. አባል
6. ከወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት የሚመለከተው ቡድን መሪ ------------------------------------አባል
7. የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩ የሚመለከተው ቡድን መሪ ---------------------- አባል
8. ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት ጉዳዩ የሚመለከተው ቡድን መሪ -----------------አባል
9. ከወሳኝ ኩነት መዝገባ ጽ/ቤት ጉዳዩ የሚመለከተው ቡድን መሪ-------------------------- አባል
10. ከሰላምና ፀጥታ ጽ/ቤት ጉዳዩ የሚመለከተው ቡድን መሪ -------------------------------- አባል
11. ከባህል፤ቱሪዝምና ጽ/ቤት ጉዳዩ የሚመለከተው ቡድን መሪ ------------------------------ አባል
12. ከፋይናንስ ጽ/ቤት ጉዳዩ የሚመለከተው ቡድን መሪ -------------------------------------- አባል
13. ከከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ጽ/ቤት ጉዳዩ የሚመለከተው ቡድን መሪ ------------ አባል
14. ከውሃ፣ማዕድንና ኢነርጂ ልማት ጽ/ቤት ጉዳዩ የሚመለከተው ማስተባበሪያ/ ቡ/ መሪ አባል
15. ከግብርና ጽ/ቤት ጉዳዩ የሚመለከተው ቡድን መሪ --------------------------------------- አባል

**የወረዳ/ከተማ አስተዳደር ቴክኒካል ኮሚቴ ተግባርና ሀላፊነት**

- በየደረጃው የተዘጋጁ ዕቅዶችን መሰረት በማድረግ የወረዳ ቴክኒካል ኮሚቴ ዕቅድ አዘጋጅቶ ለአብይ ኮሚቴ ያቀርባል፣
- በህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትና የህፃናት መብቶች ተጠቃሚነትና ተሳታፊነትን የሚያረጋግጡ አካላት ስለ ኮንቬንሽኑ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፣
- ሕብረተሰቡ ስለህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ተግባራዊነትና አፈፃፀም ግንዛቤ እንዲኖረውና በየአካባቢዉ በህጻናት ላይ የሚደርሱ የተለያዩ ጥቃቶች እንዲቆሙ ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች በየደረጃዉ ይሰራል።
- በየደረጃው የህፃናት ተጋላጭነትን በመከላከልና ተጋላጭ የሆኑ ህፃናት መብቶች ተፈፃሚነትን በመደገፍና በማቋቋም ረገድ የሚሰሩና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን የማስፈፀም አቅም ማጎልበት፣
- ከህፃናት ኮንቬንሽን ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎች ሥራ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ምርጥ ተሞክሮዎችን በማሰባሰብና በመቀመር ለሚመለከታቸው ማድረስና የልምድ ልውውጥ የጉብኝት ኘሮግራሞችን ያመቻቻል፣
- ከሚመለከታቸው የመንግሥት መ/ቤቶች፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ግንኙነት እንዲጠናከር በትብብር ይሰራል፤
- የህፃናት መብቶች ተጠቃሚነታቸውንና ተሳታፊነታቸው እንዲሁም በህፃናት የሚደርሱ ጥቃቶች በህብረተሰቡ ተሳትፎ እንዲፈታ የተለያዩ የህዝብ መገናኛዎችንና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ውጤቶችን የመጠቀም ልምድ በማስፋፋት የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ የሚያስችሉ. ተግባራትን ያከናውናል፣
- በተለያየ ደረጃ ለሚተገበረው መርሀ ግብር አስፈላጊውን የተቀናጀ የቴክኒካል ድጋፍ ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል፣ይከታተላል፣
- በየ3 ወራት የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የወረዳ/ከተማ አስተዳደር ሪፖርት ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ያዘጋጃል፣
- ከአብይ ኮሚቴ ተጨማሪ የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናሉ

2.3.5. የቀበሌ የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አደረጃጀት

የቀበሌ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

1. የቀበሌ አስተዳዳሪ-------------------------------------------------------------------------- ሰብሳቢ
2. ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሰብሳቢ----------------------------------------------ምክትል ሰብሳቢ
3. የጤና ኤክስቴንሽን-----------------------------------------------------------------------------ፀሐፊ
4. የትምህርት ተወካይ -------------------------------------------------------------------------ፀሐፊ
5. የአከባቢ ፀጥታ አስከባሪ /ሚሊሻ/ፖሊስ ተወካይ ------------------------------------------- አባል
6. የስፖርት ተወካይ-----------------------------------------------------------------------------አባል
7. የሴቶች ማህበር ተወካይ----------------------------------------------------------------------አባል
8. የእድሮች ተወካይ---------------------------------------------------------------------------- አባል
9. የልማት ባለሙያ (የግብርና ልማት ባለሙያ ) ተወካይ --------------------------------አባል
10. በቀበሌው የሚገኝ የማህበራዊ ሰራተኛ(ሶሻል ወርከር ) -------------------------------- አባል
11. የሃይማኖት ተቋማት ተወካይ(3) ------------------------------------------------------------አባል
12. የሀገር ሽማግሌ--------------------------------------------------------------------------------አባል
13. የህጻናት ተወካይ ------------------------------------------------------------------አባል ይሆናሉ፡፡

እንደ አስፈላጊነቱ ለስራዉ መቃናት የሚያግዙ ማህበረሰብ አቀፍ ተቋማትና (CBOs) ሌሎች ታዋቂ ግለሰቦችን በአባልነት ማቀፍ ይቻላል፡፡

## 2.3.6.1. የቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ኃላፊነትና ተግባራት

የቀበሌ የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለወረዳ/ለልዩ ወረዳ የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሆኖ የሚከተሉት ኃላፊነትና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. የሕጻናት መብቶች ኮንቬንሽንን አስመልክቶ ወረዳዉ በሚያወጣው መርሀ ግብር ላይ በመመስረት በቀበሌዉ ተጨባጭ ሁኔታ የቀበሌዉን ዓመታዊ መርሀ ግብር በመንደፍ ኮንቬንሽኑን ተግባራዊ ያደርጋል፤ይገመግማል፡፡በጀት ያፈላልጋል ፡፡
2. የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን በወላጆችና በህብረተሰቡ ዘንድ በቂ ግንዛቤ እንዲያገኝ የተለያየ ስልቶችን በመቀየስ ትምህርት ይሰጣል፡፡
3. በህፃናት ላይ የሚደርሱ በደሎችና ጥቃቶችና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች መፍትሄ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣
4. ለህፃናት ሁለንተናዊ እድገት የሚያግዙ በትምህርት፣በጤና፣በባህል፣በማህበራዊ ኑሮ በስነ ልቦናና በኢኮኖሚ ረገድ ጥናቶች እንዲካሄዱ ሀሳብ ያቀርባል፣በጥናቱም ይሳተፋል፡፡
5. ለህፃናት አገልግሎት የሚሰጡ ንባብ ቤቶችን፣የስፖርት ማዘወተሪያ ስፍራዎችን፣መዝናኛዎችን፣ወዘተ የሚደራጁበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡
6. በህፃናት ዙሪያ የወጡ የህግና ፖሊሲ ማዕቀፎች ላይ ህብረተሰቡና ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያደርጋል-
7. ለህፃናት መብቶችና ደህንነት መጠበቅ ፋይዳ ያላቸው የተለያዩ የድጋፍና እንክብካቤ ስራዎችን ይሰራል፣ ያስተባብራል ፡፡
8. በህፃናት ዙሪያ ከሚሰሩ ተቋማት/ድርጅቶች ጋር የትብብርና ቅንጅታዊ መድረኮች እንዲፈጠሩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡ አገራችን ተቀብላ የፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና በአገራችን ፖሊሲዎችና ህጎች የተካተቱ መብቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡
9. ህፃናት በሁለንተናዊ መልኩ የመብታቸውና የደህንነታቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ አመቺ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፡፡
10. ሕፃናት ድምፃቸውን እንዲያሰሙና መብትና ደህንነታቸውን ለማስጠበቅ የተለያዩ አደረጃጀቶችን ማለትም የህፃናት ምክር ቤት በማቋቋምና ክበባትን በት/ቤቶች በማጠናከር ይሠራል፡፡
11. ለችግር የተጋለጡ ህፃናት አስፈላጊውን ድጋፍና እንክብካቤ እንዲያገኙ ይሠራል፣ ያስተባብራል፡፡
12. በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ሕፃናት ወደ ጎዳና እንዳይወጡ ቅድመ መከላከልና ወደ ጎዳና የወጡ ህፃናትን ወደ ቤተሰብ መቀላቀልና እንዲዋሃዱ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡
13. ህፃናትን በተመለከተ መረጃ ያደራጃል፣ ያሰራጫል፡፡
14. ስለ ኮንቬክሽኑ ጽንሰ ሃሳብ ሕብረተሰቡን ለማስተማር የሚያስችሉ ስልቶችን በመንደፍ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

15. የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን በተጠናከረና በተቀነባበረ መልኩ ተግባራዊ እዲሆን የተለያዩ ዘዴዎችን ይቀይሳል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፡፡
16. የቀበሌዉን የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የስራ አፈፃጸምን አስመልክቶ በየ 3፣6፣ 9 ወርና እና በአመት ሪፖረት ያዘጋጃል ፣ ለሚመለከታቸዉ አካላትም ያስተላልፋል፡፡ በአመት ሁለት ጊዜ ከባለድርሻ አካላት ጋር የእቅድ አፈጻጸም ግምገማ ያደርጋል፡፡ ዓመታዊ የዕቅድ ክንውን ሪፖርት ለወረዳ/ልዩ ወረዳ የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፣ ያቀርባል፡፡
17. ህፃናትን የሚጎዱ ባህሎችና ልምዶች እንዲወገዱ ለህብረተሰቡ ባመቸው መንገድ ሁሉ ትምህርት ይሰጣል፡፡
18. በህጻናት ላይ ጥቃት እንዳይደርስ አስፈላጊዉን መከላከል ያደርጋል ፡፡ጥፋት ተፈጽሞም ከተገኘ አጥፊዎችም በአስቸኳይ ለህግ እንዲቀርቡ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡
19. የክትትልና ግምገማ ስርአት ይዘረጋል፡፡

### 2.3.6.2. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት፣

1. የኮሚቴዉን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል፡፡ ኮሚቴዉን ይወክላል፡፡
2. የኮሚቴዉን ጽ/ቤት በበላይነት ይቆጣጠራል፡፡
3. ኮሚቴዉ የሚያደርገዉ የደብዳቤ ልዉዉጦች ላይ ይፈርማል ፡፡
4. ኮንቬንሽኑን አስመልክቶ መንግስት የሚያወጣቸዉን መመሪያዎችና ኮሚቴዉ የሚያስተላልፋቸዉን ዉሳኔዎች ተግባራዊ ያደርጋል፣አፈፃፀማቸዉንም ይከታተላል፡፡
5. የኮሚቴዉ ስራ እንዲቃና አስፈላጊዉን ሁሉ ያደርጋል፡፡
6. እንደአስፈላጊነቱ ኮሚቴዉ የሚሰጠዉን ሌሎች ተግባራት ያከናዉናል፣
7. ከልዩ ወረዳ/ወረዳ/ከተማ የህጻናት መብቶች ኮንቬንሽን የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚሰጡትን ተጨማሪ ተግባራት ያከናውናል፡፡

### 2.3.6.3. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ ተግባርና ሃላፊነት

1. ሰብሳቢው በማይገኝበት ጊዜ ሰብሳቢውን በመወከል ኮሚቴውን በበላይነት ይመራል
2. ሰብሳቢው ከሌለ የኮሚቴውን ሰብሰባ በሊቀ መንበርነት ይመራል
3. ለኮሚቴው የሚቀርቡ ጉዳዮችን ከጸሀፊው ጋር በመሆን ቅደም ተከተል በማውጣት ለውይይት እንዲቀርቡ ለሰብሳቢው ያቀርባል
4. ኮንቬንሽኑን አስመልክቶ መንግስት የሚያወጣቸውን መመሪያዎችና ኮሚቴው የሚያጸድቃቸውን ወሳኔዎች ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፡፡
5. በየደረጀው የሚገኙ የህጸናት መብቶች ኮንቬንሽን የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች እንዲጠናከሩ እገዛ ያደርጋል
6. የኮሚቴው ስራ እንዲቃና አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል
7. ሰብሳቢው የሚሰጣቸውን ሌሎች ተግባራት ያከናወናል፡፡

2.3.6.4. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ፀሃፊ ተግባርና ኃላፊነት

1. የኮሚቴውን ጽ/ቤት ያደራጃል፣ ደብዳቤዎችን አርቅቆ ለሰብሳቢው ያቀርባል፣ስርጭታቸዉንም ይከታተላል ።
2. ከምክትል ሰብሳቢው ጋር በመሆን የስብሰባ አጀንዳዎችን አዘጋጅቶ ለሰብሳቢው ያቀርባል፣ ቃለ- ጉባኤ ይይዛል፡፡
3. የኮንቬንሽኑን አፈፃፀም አስመልክቶ ከወረዳና ከከተሞች/ቀበሌዎች ህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል መ/ቤቶችና ከየዞኑ ኮሚቴዎች የሚላኩ ሪፖርቶችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላትም ያሰራጫል፡፡
4. ኮንቬንሽኑን በሚመለከት የሚወጡ አዋጆችን፣ መመሪያዎችን፣ ደንቦችንና ማቴሪያሎችን ለሚመለከታቸው ክፍሎች ያሰራጫል፡፡
5. የኮሚቴው ስራ በሚመለከት ከሰብሳቢውና ከምክትል ሰብሳቢው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ክፍል ሦስት

### 3.1. ዕቅድ፣ክትትልና ግምገማ የመረጃ አያያዝ

የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ወደፊት ሊያሳካ የሚፈልገውን ውጤት ዛሬ ላይ ሆኖ ማስቀመጥ ብቻ ሳይሆን ወጤቱ ሊገኝ የሚችልበትን መንገድ(ስልት) ጭምር ማቀድ ይኖርበታል፡፡ ዕቅዱ የህጻናትን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ፍላጎቶች ለማሟላት፣ የጋራ ራዕይን፣አላማና ግቦችን፣እንዲሁ ግቦቹን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ስልቶችን ወይም እስትራቴጂዎችን እና ለሥራው የሚያስፈልጉ ግብአቶችን / የሰው ሀይል፣የማቴሪያል የገንዘብ አቅምንና ጊዜን/ መሠረት በማድረግና በማቀናጀት የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት እንዲረዳ የሚዘጋጅ ነው፡፡

ከዚህ አንፃር የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ተጨባጭ የሆነ የየአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ በጊዜና በዉጤት የሚለካ እቅድ ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

### 3.2. ዕቅዱ ሊኖረው የሚገባው መሰረታዊ ጉዳዮች

- ልናሳካው በምንፈልገው ጉዳይ ዙሪያ አሁን ያለንበት ሁኔታ ምን ይመስላል የሚለው ሲሆን ይህም በዕቅድ መግቢያ ላይ በሀተታ ይገለጻል(ቅድሚያ ልናተኩርባቸው የሚገቡ አንገብጋቢ ሕፃናት ተኮር ጉዳዮች፣የችግሮቹ ስፋትና መንስኤዎቻቸው መለየትና ባጭሩ መገለጽ ያለበት ሆኖ ከዞን ዞን፣ከወረዳ ወረዳ፣ከከተማ ከተማ እንደ ችግሮቹ አንገብጋቢነት ቅድሚያ የምንሰጠው ጉዳዮች ሊለያዩ ይችላሉ)

- ለወደፊት ልንደርስበት የምንፈልገውን ደረጃ ግብ /objectives/ መግለጽ ይኖርበታል፡፡

- እዚህ ደረጃ ላይ ለመድረስ መፈጸም የሚያስፈልገንን(እንደ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) ተግባር እና ዘዴ ማስቀመጥ ያስፈልጋል/ strategies / (ይህ ክፍል በአባል መ/ቤቶችና በኮሚኒቴው በቅንጅትና በአጋርነት ሊሰሯቸው የሚችሎ ተግባራት እና አገልግሎቶች ላይ ማተኮር ያስፈልጋል፡፡)

- የዕቅዱ የተፈፃሚነት ወሰን በግልጽ መቀመጥ አለበት( በዕቅዱ ተጠቃሚ የሚሆኑ ወገኖች፣በዕቅዱ አፈፃፀም ተሳታፊ የሚሆኑ አካላት፣ጥቅም ላይ የሚውሉ ስልቶች፣አስፈላጊ ግብአቶች፣እቅዱ የሚፈጸምበት ጊዜ ወዘተ ያጠቃልላል)፡፡

**ክትትል**/monitoring/

የሕፃናት መብቶች መከታተል ማለት ቀጣይነት ያለውና በየጊዜዉ በሥርዓት የሚመራ በሕፃናት መብት ላይ የሚሰሩ ስራዎችን በተመለከተ መረጃ የመሰብሰብ፤የመመርመርና ሪፖርት ማድረግ ሂደት ማለት ነው፡፡መከታተል ጠንካራና ደካማ ጎኖችን መለያ እና ለሚመለከታቸው አካላት ትክክለኛውን ውሳኔ እንዲያሳልፉና እርምጃ እንዲወስድ ለማገዝ አጥጋቢ መረጃ ማቀበያ መሳሪያ ነው፡፡ በአጠቃላይ የሕፃናት መብት መከታተል የሚከተሉትን ተግባራት ያጠቃልላል፡፡

- ምሉዕ የሆነ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋትና መፈጸም
- ለውጦችንና እድገትን የመመርመር ፤የማገዝና ዶክመንት ማድረግ
- ለቀጣይ እርምጃ የሚያዘጋጅ ጥናቶችንና ሪፖርቶችን አዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው ማቅረብ ሲሆን በክልላችን የሚደረገው የሕፃናት መብት አፈፃፀም ክትትል ቀጣይነት ያለው፤ተፈፃሚ፣ተደራሽ የሚሆንና ለክልሉ የፖሊሲና የፕሮግራም እቅዶች መጋቢ የሚሆን መሆን አለበት፡፡ በመሆኑም የሕጻናት መብት አፈፃፀም ክትትል ማለት የመብት ጥሰቶች ላይ ማተኮርና ማውገዝ ብቻ ሳይሆን በሕጻናት ላይ የክልሉን ገጽታ ለመለወጥ የሚያስችሉ ፕሮግራሞችን ለመንደፍ እንዲቻል አስፈላጊዉን መረጃ መሰብሰብ፤ማጠናቀርና ሪፖርት ማድረግን የሚያጠቃልል ሂደት መሆን አለበት፡፡ በአጠቃላይ የሕጻናት መብትን ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረት ክትትል እንደ አንድ ቁልፍ ተግባር መወሰድ ያለበት ሦስት መሰረታዊ ዓላማዎችን በመያዝ ነው፡፡እነዚህም፡-

- መንግስትን በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚጠበቅበትን ግዴታ ለመወጣት ማስቻል
- በሂደት የሚመዘገቡ የሕፃናት መብት አፈፃፀም ውጤቶችን፤ ለውጦችንና መሻሻሎችን ለማሳየት
- የሕፃናትን መብት አፈፃፀም በተመለከተ ለማቀድ፤ለመተግበርና ለመገምገም የሚያስችል ስርዓት ያለው ክልላዊ የሕፃናት ሁኔታ መረጃ እንዲኖር ለማድረግ ናቸው፡፡

### የክትትል የትኩረት ነጥቦች

የክልል፤የዞን፤የልዩ ወረዳ ፤የወረዳ ፣ የከተማ አስተዳደርና የቀበሌ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎች በየደረጃው መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅቶች የእምነት ተቋማት እና ህብረተሰቡ በሕፃናት ዙሪያ የሚያካሂዱትን ፕሮጀክት፤ፕሮግራሞችንና ዕቅዶችን ቀጥሎ በተዘረዘሩት የክትትል መሪ መስፈርቶች መሰረት በዋነኛነት ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡

- ተከታታይነት ያለው ወቅታዊ የፕሮጀክት፤የፕሮግራም ወይንም የእቅድ አፈፃፀም ዕድገት (progress) በተጠናከረ መልኩ መከታተል፡፡
- በፕሮጀክቶች፤በፕሮግራሞችና በዕቅዶች ግብዓት፤በዝርዝር የስራ አፈፃፀም፤በግዜ ሰሌዳ እና በውጤት ላይ ያተኮረ የክትትል ስራ ማካሄድ፤
- ተከታታይነት ያለው የመረጃ ልውውጥ(feedback) በማድረግ የፕሮጀክቶች፤የፕሮግራሞችና የዕቅዶች ውጤታማነት( effectiveness) እና አዋጭነትና ብቃት( efficiency) ላይ የተመሰረተ መሆኑን በመከታተል ማስፈፀም፤
- ችግሮችን በወቅቱ ደርሶ የመለየት ( problem identification) ከእቅድ ውጭ የሆኑትን በማረም (correction of deviation)የከፋ ችግር እንዳይፈጠር መፍትሄ በመፈለግና የማስተካከል ሚና መጫወት
- ከሕፃናት ጋር የሚያያዙ ጥቆማዎች/ጥያቄዎች በተገቢው ሁኔታና በጊዜ ምላሽ ማግ ኘታቸውን መከታተልና መረጃ መለዋወጥ

### የግምገማ / evaluation/ አቅጣጫዎች

- በሴክተሮች በሕፃናት ዙሪያ በሚሰሩ ፕሮጀክቶች፤ፕሮግራሞችና እቅዶች ላይ የተገኘውን ውጤት (Output) ፋይዳ (Impact) እና በእሴቶቻቸው ላይ ትኩረት አድርጎ መገምገም፤
- በሴክተሮች በሕፃናት ዙሪያ የሚሰሩ ፕሮጀክቶች ፤ፕሮግራሞችና እቅዶች የያዟቸውዓላማዎች ምን ያህል ግባቸውን እንደመቱጠቀሚታቸውን(relevance)፤ስኬታማነታቸው (effectiveness) አዋጭነታቸውንና ብቃታቸውን (efficiency) ከሕፃናት ወቅታዊ ፍላጎትና ችግሮች ዙሪያ በመፈተሽ የውሳኔ ኃሳብ ለሚያስተላልፈው የበላይ አካል ማቅረብ
- በሕፃናት ዙሪያ የሚሰሩ ፕሮጀክቶች፤ፕሮግራሞችና መደበኛ የክንውን እቅዶች ላይ የሂደት ግምገማ(mid-term rieview ) ወቅት በተገኘው ጭብጦች ላይ በመመስረት ማጠቃለያ ግምገማ ማካሄድ

- በሕጻናት ዙሪያ የሚሰሩ ፕሮጀክቶች፣ፕሮግራሞችና እቅዶች ላይ የተገኙ ውጤቶች ዘላቂነትን (sustaiability) የሚያረጋግጡ፣ክንዋኔዎች ደካማና ጠንካራ ጎኖችን በማመዛዘን ( SWOT analysis ) በመለየት የሚያመለክት ግኝት ማካሄድ
- በሕጻናት ዙሪያ የሚሰሩ ፕሮጀክቶች፣ፕሮግራሞች እና እቅዶች የማስፈጸሚያ ወጭአቸው በአካባቢው የማመንጨት አቅም ስርዓት መፈጠሩንና ከሚመለከታቸው ሴክተር መ/ቤቶች ጋር በማጣጣም(በሰው ሃይል፣በአደረጃጀትና በቴክኒክ)ተካቶ ለመስራት የሚያስችል ተቋማዊ መሰረት መኖሩን ማረጋገጥ

**መረጃ ስለመያዝና ስለማስተላለፍ/ documentation and reporting /**

አሁን ባለንበት የመረጃ ዘመን ያለ መረጃ የሚሰራ ነገር የለም ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ የህዝብን ጥያቄና ፍላጎት ለመመለስ የሚያስችል ዕቅድ ለማቀድ መሰረታዊ ግብአት ነው ማለት ይቻላል፡፡ በክልላችንም ሆነ በአገራችን መረጃ የመያዝም ሆነ በአግባቡ የማስተላለፍ ችግር በሰፊው ይስተዋላል፡፡ መረጃ አጠናቅሮ መያዝና ማስተላለፍ በአሁኑ የመረጃ ዘመን ላይ ብዙም የማይከብድ ስራ ቢሆንም ጠቀሜታው ግን በጣም ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነው፡፡ የመንግስትን ፖሊሲ ለመቅረጽም ሆነ ለተለያዩ የህፃናት ጉዳዮች ማስፈጸሚያ በጀት ለመበጀት፣የት የት ቦታ ችግሩ እንደሚብስ ለመለየት፣ችግሩን ለመቅረፍ እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎችና መልካም ተሞክሮዎችንም ሆነ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን ለማወቅ መረጃ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው ፡፡

የሕፃናት መብት ኮንቬንሽን የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትም እርስ በርሳቸውም ሆነ ከሌሎች የመንግስት አካላት ጋር መረጃ ለመለዋወጥ የሚያስችል የተለያዩ ስልቶችን ነድፈው መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል፡፡ይህ ስልት መረጃን ለመሰብሰብ፣ተደራሽ ለማድረግ፣ለመመርመር/ለማገናዘብና ለመለዋወጥ ምን ዓይነት ስርዓትና ዘዴ መጠቀም ያስፈልጋል የሚለውን የሚመልስ መሆን ይኖርበታል፡፡ ለምሳሌ መረጃን በስልክ፣በደብዳቤ፣በአካል በመገኛኘት(በኢ-መደበኛ ወይም በመደበኛ መንገድ)፣መረጃ መለዋወጫ መድረክ/ስብሰባ በማዘጋጀት ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡

ሕፃናት ተኮር መረጃዎችን በተደራጀና ተደራሽ በሆነ ሁኔታ መሰብሰብ፣መተንተን፣ማደራጀትና ማሰራጨት ሕፃናት መብታቸውን ሙሉ በሙሉ እንዲጠቀሙ ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ከዚህ ውጭም ከኮሚቴው አባላትም ይሁኑ ሌሎች ተቋማት መረጃ በየጊዜው መደበኛ በሆነ መንገድ እንዲያቀርቡ የሚያበረታታ አሠራር ሊኖራቸው ይገባል፡፡በዚህ መልኩ የሚሰበሰቡ መረጃዎች አንድ ላይተጠቃለው ተደራሽ የሚሆኑበት ሁኔታ መፈጠር ይኖርበታል፡፡

ከመረጃ አያያዝ ጋር በተያያዘ ሁሌም ሊታወስ የሚገባው መልካም/ምሳሌ የሚሆኑ/ተሞክሮዎችን ለመለየትና በሌሎች አካባቢ ለሚገኙ ኮሚቴዎች ማስተላለፍም ጭምር ላይ ነው፡፡በየዞኖች፣ወረዳዎች፣ከተማ አስተዳደሮች እና ቀበሌዎችም ጭምር ፈጠራ የታከለባቸውና በጣም ጠቃሚ ተሞክሮዎች ሲኖሩ መረጃዎችን በተደራጀ መንገድ በመያዝ ለሌሎች ልምድ እንዲሆኑ መሰራጨት ይኖርባቸዋል፡፡

በአጠቃላይ በየደረጃዉ የሚገኙ የህጻናት መብት ኮንቬንሽን ኮሚቴዎች መረጀዎችን በአግባቡ ማደራጀትና ለሚመለከታዉ አካል ወቅቱን ጠብቀዉ ማስተላለፍ የሚጠበቅባቸዉ ሲሆን አፈጻጸማቸዉን በተመለከተ በየሩብ አመቱ ሪፖርት በተዋረድ ለመዋቅራቸዉ የሚያቀርቡ ሲሆን በግማሽ አመትና በበጀት አመት መጨረሻ የተጠቃለለ ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡

## ክፍል አራት

## የሕጻናት መብቶች ኮንቬንሽን የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሰራ ዘመን፣ የበጀት ዓመት መመሪያ ስለማሻሻል

### 1.1 የኮሚቴው የስራ ዘመን

የኮሚቴው አባላት የሥራ ዘመን የኮሚቴው አደረጃጀት እስካለ ድረስ የሚቀጥል ሆኖ ከኮሚቴው አባላት መካከል ከየ/መቤቱ/ ተቋማቱ የተወከሉ አባላት አሳማኝ ምክነያቶች ሥራቸውን መቀጠል ካልቻሉ የወከሉአቸው ተቋማት በእነሱ መትክ ሌላ ሰው የመወከል ግዴታ አለበቸው፡፡

### 1.2 የበጀት ዓመት


ኮሚቴው የሚጠቀመው የኢትዮጲያን የዘመን አቆጣጠር ሲሆን ይህም አንድ የበጀት ዓመት ከሀምሌ 1- ሰኔ 30 ያለውን ጊዜ የሚያካትት ይሆናል

### 1.3 መመሪያ ስለ ማሻሻል

መመሪያው እንደ አስፈላጊነቱ በክልሉ ሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ቢሮ አማካኝነት ሊሻሻል ይችላል፡፡

-------------------------

**የማዕከላዊ ኢትዮጲያ ክልል መንግስት ሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ቢሮ**


የክልል ሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ቢሮ
የክልል የሕጻናት መብቶች ኮንቬንሽን የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ
የዞን/ የከተማ/የልዩ ወረዳ የክልል የሕጻናት መብቶች ኮንቬንሽን የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ
የከተማ /የወረዳ/ክ/ከተማ የሕጻናት መብቶች ኮንቬንሽን የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ
የቀበሌ የሕጻናት መብቶች ኮንቬንሽን የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ

**ዋቢ መጽሃፍት**


1. የማዕከላዊ ኢትዮጲያ ክልል መንግስት ፕላን ኮሚሽን /2016ዓ.ም/
2. የሴቶችና ህጻናት መብት ጥበቃ የማስተማሪያ ማንዋል /2001 ዓ.ም/
3. አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ሰነዶች /1999 ዓ.ም/
4. የፌደራልና የክልሉ ህገ መንግስት
5. የተሻሻለው የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት የአስፈፃሚ አካላትንሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 178/2011
6. የተለያዩ ድህረ ገጾች/https://www.statsethiopia.gov.et/population-projection/